ወርኃዊ ጥንቅር፣ ቁጥር. 009
ጥቅምት 2018 ዓ.ም.



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

BRIDGE Research & Innovation-
Parliaments. Peace. Policy

+251 911 86 12 34
+251 115 57 74 96
research@bridge-et.org
https://bridge-et.org/
150096, Addis Ababa, Ethiopia.
Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.

## መልክዓ-ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው። ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው።

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፦ ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ፡፡
- አዲስነት፦ ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፦ ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

በኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል










## ማውጫ

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ........................ 2
የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባሮች............ 6
የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር...................... 7
የእንደራሴዎቹ የውክልና ሥራ....................... 11
የፓርላማ ዲፕሎማሲ.................................. 12
እንደራሴዎቹ ስለ'ራሳቸው በ'ራሳቸው............. 14
ታላቁ ቀን............................................ 16
የብሪጅ አጭር ዳሰሳዊ ምልከታ በእንደራሴዎቹ ውክልና ዙሪያ................................................ 17

# በወሩ የተካሄደ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ

ስድስተኛው የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የመጨረሻው የሆነውን የሥራ ዘመን ኹለተኛ ወሩን ያሳለፈው ተለምዷዊዎቹን ሕገ-መንግሥታዊ ኀላፊነቶቹን በመወጣት ነበር። በቀደመው መስከረም ወር የመክፈቻ ንግግራቸውን ለኹለቱም ምክር ቤቶች ያቀረቡትን የፕሬዝደንት ታዬ አጽቀ ሥላሴን የ2018 ዓ.ም. የትኩረት አቅጣጫ የውሳኔ ሐሳብ ያጸደቀው ምክር ቤቱ፣ በዚኹ እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ አሉኝ ያላቸውን ማብራሪያ የሚሹ ጥያቄዎች ለጠቅላይ ሚኒስትሩም አቅርቦ የመንግሥትን ምላሽ አድምጧል። ምንም እንኳን፣ በዚኹ ወር ላይ ምክር ቤቱ ያጸደቃቸውም ሆኑ ወደ ቋሚ ኮሚቴዎች የመራቸው ሕግጋት ባይኖሩትም፣ ሰፋ ያሉ የአስረጂ መድረኮችን አከናውኗል። ይኽች የወርኃ ጥቅምት የእንደራሴ ዕትምም፣ የጠቅላዩን ዋና ዋና የንግግር ሐሳቦች አጠቃሎን ጨምሮ፣ ምክር ቤቱ በወሩ ያካሄዳቸውን ጉዳዮች ትዳስሳለች፤ ከዚኽ ባለፈም፣ በእንደራሴዎቹ የውክልና ሥራ ስኬቶች እና ተግዳሮቶች ዙሪያ አጭር ዳሰሳዋን ይዛ ቀርባለች።

ጥቅምት 18

**የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በወርኃ ጥቅምት አንድ መደበኛ ስብሰባ አካሂደዋል።**

**አጀንዳ 1**

**በዚኽ ጥቅምት 18 2018 ዓ.ም. ባካሄዱት 6ኛው ዙር 5ኛ ዓመት 2ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ፣ ከእንደራሴዎቹ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የመንግሥታቸውን አቋም እና ምላሾች ሰጥተዋል።**

**አጀንዳ 2**

**ከዚኽ በተጨማሪም፣ በዚያው መደበኛ ስብሰባቸው፣ መስከረም 26 2018 ዓ.ም.፣ በፕሬዝደንት ክቡር ታዬ አጽቀ ሥላሴ የቀረበውን የ2018 የመንግሥት የትኩረት አቅጣጫ የድጋፍ ሞሽን ውሳኔ ቁጥር 1/2018 አድርጎ በአንድ ድምፀ ተአቅቦ በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል።**

# ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ ወርኃ ጥቅምትን ያገባደዱት፣ በፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ክንውኖቻቸው አልያም በዛ ባሉት የአስረጂ መድረኮቻቸው ብቻ አልነበረም፤ ከዚያ ሻገር ብለውም፣ የአገሪቷ ርዕሰ-መንግሥት ወደ አዳራሹ እንዲመጡ ሆኖ፣ ያሳስቡናል ያሏቸውን በዛ ያሉ ጥያቄዎች አንስተው ምላሽ እና ማብራሪያ በመጠየቅም ነበር።

እንደራሴዎቹም፣ ከሰነበተው የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ እስከ ሰሜኑ ፖለቲካዊ ውጥረት፣ ከኢትዮጵያ የብድር ክፍያ እስከ የአገር ቤት የጸጥታ ኹኔታ የደረሱ ጥያቄዎቻቸውን ለገዢው ፓርቲ ፕሬዝደንት አንስተውላቸው ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድም፣ ሰፋ ያሉ ሰዐቶቻቸውን የወሰደባቸውን የባሕር በሩን ጥያቄ ጨምሮ፣ የዐብይ ኢኮኖሚውን አኹናዊ ኹኔታ እና ታጣቂዎቹ ሰላማዊ ፖለቲካን ይጀምሩ ዘንድ መንግሥታቸው ዛሬም ዝግጁ መሆኑን ያከሉ ምላሾቻቸውን እና ማብራሪያዎቻቸውን አስደምጠዋል። ይኽች የእንደራሴ ዕትምም፣ ከጠቅላዩ ማብራሪያዎች የዋንኞቹን ርዕሰ-ጉዳዮች እንደሚከተለው አሳጥራ ይዛለች።



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ ማብራሪያ በሰጡበት ዕለት፤

## የአገር ቤቱ ፖለቲካ

ጥቅምት 18 2018 ዓ.ም. ማለዳ ወደ ሕዝብ ተወካዮቹ አዳራሽ የደረሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ፣ ከተናገሩባቸው ርዕሰ-ጉዳዮች መካከል አንዱ የአገር ቤቱን ፖለቲካ አስመልክቶ መንግስታቸው ያለውን አኹናዊ አቋም ነበር። በሰላማዊ መንገድ መታገል ለሚፈልጉ ኀይሎች የመንግስት በር ክፍት ነው ሲሉ ዛሬም የተሰሙት ጠቅላይ ሚንስትሩ፣ የኢትዮጵያን ዕድገት እና ብልጽግና የማይፈልጉ ባዕዳን፣ በጦርነት እንደማያሸንፉ ስለሚያውቁ በቅጥረኞች እና በተላላኪዎች ምኞታቸውን ለማሳካት ቢጥሩም አይሳካላቸውም ብለዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ ችግር አለብኝ የሚል ኃይል ኹሉ ችግሩን በሰላማዊ መንገድ መጠየቅ እንዲችል መንግስት ጽኑ ፍላጎት እንዳለው ሲናገሩ የተደመጡት የተከበሩ ዶ.ር. ዐቢይ፣ ከዚኽ በፊት የታጠቁ ኃይሎች የሰላምን አማራጭ በመከተል ከመንግስት ጋር ለአገራቸው ዕድገት አብረው እየሰሩ መሆኑን አስረድተዋል። ‘መንግስት ዛሬም ለሰላማዊ ንግግር ዝግጁ ነውን?’ ለሚሉት እና ተያያዥ የእንደራሴዎቹ ጥያቄዎች የመለሱት ጠቅላዩ፣ ፖለቲካዊ ልዩነቶችን በንግግር ለመፍታት እና ለሰላም አኹንም መንግስታቸው ዝግጁ መሆኑን ዳግም ጠቅሰው፤ በድርድር መፍትሔ የማያገኙ ላሏቸው ጉዳዮች በአገራዊ የምክክር ሂደት እና በሽግግር ፍትሕ መፍትሔ ለማበጀት አማራጮች እንዳሉ ተናግረዋል። በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ጥያቄ አለኝ የሚል ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሰላም እና በድርድር፣ በሕዝበ- ውሳኔ ችግሮቹ እንዲፈቱ ሊጥር ይገባል ያሉት ጠቅላይ ሚንስትሩ፣ በዚኽ ጉዳይ መንግሥት ጽኑ ፍላጎት እንዳለውም ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል። ኢትዮጵያ በኹለት እግሯ መቆም እንዳትችል የሚሹ አገራት ባሉበት ኹኔታ፣ በአገሪቱ የተረጋጋ ሁኔታ ማምጣት አስቸጋሪ መሆኑን ያነሱት ዶ.ር ዐቢይ፣ ኢትዮጵያ አኹን ባለችበት ተጨባጭ ኹኔታ ለመገንጠልም ሆነ ለመጠቅለል ምቹ አይደለችም ሲሉም ተደምጠዋል።



ኣንደራሴዎቹ የጠቅላዩን ማብራሪያ በማድመጥ ላይ ፤

የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ የዕለተ ኀሙስ ውሎ፣ ወደ ሰሜኑ ፖለቲካም የተኬደበት ነበር። በሕወሓት እና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ እንደራሴዎቹ ላነሷቸው ጥያቄዎች ሰፋ ያሉ ምላሾችን የሰጡት ጠቅላይ ጦር አዛዡ፣ ሕወሓት የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነትን ባለማክበር እንዲኹም ከፌደራል መንግሥቱ የሚላክን በጀት ለልማት ሥራዎች ከማዋል ይልቅ ለወታደራዊ እንቅስቃሴዎች ስለማዋሉ አንስተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማብራሪያቸው፣ መንግስታቸው በትግራይ ክልል ውስጥ ተጨማሪ ውጊያ እንደማይፈልግ ያነሱት የተከበሩ ዶ.ር ዐቢይ፣ የመንግስታቸው ትኩረት አገሪቱን በጋራ በማልማት ላይ መሆኑን አጽንዖት ሰጥተው ሲናገሩ ተደምጠዋል። መንግሥትን በኃይል የመጣል ማንኛውም ሙከራ ፈጽሞ እንደማይሳካ ሲናገሩ የተሰሙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ፣ በትግራይ ዘላቂ ሰላም ሊመጣ የሚችለው ትጥቅ በመፍታት፣ በሪፎርም እና በትብብር ብቻ መሆኑን፤ ይኽም የመንግስታቸው አቋም እንደሆነ በድጋሚ ግልፅ አድርገዋል። "በፌደራል መንግሥት ለትግራይ ክልል የተመደበው በጀት ሙሉ በሙሉ በልማት ላይ ሳይሆን ለወታደራዊ እንቅስቃሴዎች እየዋለ ነው፤ ይኽም ትክክል አይደለም" ያሉት የብልጽግና ፓርቲው ፕሬዝደንት፣ ትግራይ ልማት እንደሚያስፈልጋት እና ለዚኽም በሰላማዊ መንገድ መሥራት እንዳለባት ሲያሳስቡ ተሰተውለዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ በትግራይ ለሰላም ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች ሲያብራሩም፣ የታጠቁ ቡድኖችን ትጥቅ ማስፈታት፣ የሕዝብ አገልግሎቶችን ማስጀመር፣ የተፈናቀሉ ዜጎችን መመለስ እና የውጭ ግንኙነት የመምራት ሥልጣን የፌደራል መንግሥቱ ብቻ ነው የሚለውን ሕገ-መንግሥታዊ መርህ መከተል የሚሉትን ዘርዝረዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለውም፣ ሕወሓት የሰላም ሂደቱን የሚያሰናክሉ እንደ የጦር መሳሪያ ኮንትሮባንድ ማዘዋወር እና ያልተፈቀደ የውጭ ግንኙነት መፈጸም ያሉ ተግባራትን ቀጥሏል ሲሉም ግንባሩን ወቅሰዋል። የፕሪቶሪያው ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን በከፍተኛ ድምፅ የሚጠይቁት አካላት አንዳንዶቹ የድርድሩ ሂደት አካል አልነበሩም ያሉት ጠቅላዩ፣ "ፕሪቶሪያን የተደራደርነው ከጄነራል ጻድቃን፣ ጌታቸው ረዳ እና አሰፋ አብርሃ ጋር ነው። ዋነኞቹ ተደራዳሪዎች እነዚህ ናቸው" ሲሉም የፈራሚዎቹን ማንነት ለእንደራሴዎቹ አስታውሰዋቸዋል። ጠቅላዩ ለጥቀውም፣ "እነሱን ስጠይቃቸው ያሉኝ ነገር አለ። ነገር ግን በቦታው ያልነበሩት ፕሪቶሪያን የማያውቁት ሰዎች ፕሪቶሪያን እናስከብራለን ይላሉ። የወለደችው እያለች የታቀፈችው እናት ልሁን አለች እሱ ነው" ሲሉም ተሰምተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለ ሕወሓት ሕጋዊ ሰውነት ሲናገሩም፣ ቡድኑ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንደገና በመመዝገብ ሕጋዊነቱን መመለስ እንደሚችል ገልጸዋል። አያይዘውም ሕወሓት በዋነኛነት የሚጠበቅበት የምርጫ ቦርድን ደንብ ማክበር፣ ሕገ-መንግሥቱን ማክበር እና ሕጋዊ ፓርቲ ለመሆን ጉባኤ ማካሄድ ነው፤ ይኽ ደግሞ አስቸጋሪ ነገር አይደለም ሲሉ ተናግረዋል።

## "ኢትዮጵያ ዕዳ የመክፈል ችግር የለባትም"

ሣሥተኛው የሪፐብሊኩ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ በ6ኛው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን ውሏቸው፣ ስለ አገሪቷ ኢኮኖሚያዊ ኹኔታም የመንግስታቸውን ቀጣይ ሂደቶች አሃዞችን አስደግፈው ሰፊ ማብራሪያዎችን ሰጥተዋል። ግብርና መር ኢኮኖሚ ብቻ አገርን ማሳደግ እና መለወጥ ስለማይችል፣ ብዝሓ ዘርፍ መር የኢኮኖሚ አማራጮችን በመከተል እና በመንደፍ የአገርን ዕድገት ማሳደግ እንደሚቻል የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ግብርና ለኢንዱስትሪው ግብዓት እንዲያቀርብ በተሰራው ሥራ ውጤታማ ሥራ መሰራት መቻሉን አስረድተዋል። ብዝሓ ዘርፍ ኢኮኖሚያዊ አማራጮችን መከተል በግብርናው፣ በኢንዱስትሪው እና በማዕድን ዘርፉ ምርት እና ምርታማነት በማሳደግ እንዲኹም የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማስፋት እና በማስተሳሰር የአገር ዕድገት ለማፋጠን በትኩረት እየተሰራ እንደሚገኝም ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል። ዓመት የተሻገረው የዐብይ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራን በዚኹ ማብራሪያቸው ያነሱት ጠቅላዩ፣ ኢትዮጵያ የተገበረችው የኢኮኖሚ ማሻሻያ የአገሪቱን ፋይናንሺያል ተቋማት ከውድቀት የታደገ ነው ብለዋል። ለአብነትም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አንዱ ከሞት የዳነ ተቋም መሆኑን ያነሱት ዶ.ር. ዐቢይ፣ መንግስት በ2017 በጀት ዓመት አይቻሉም የተባሉትን ጉዳዮች በተግባር ፈጽሞ ያሳየበት እና ለሕዝብ ቃል የገባቸውን ጉዳዮች በፍጥነት እና በውጤት ተግብሮ ያሳየበት የስኬት ዓመት እንደነበር ገልጸዋል፡፡



እንደራሴዎቹ የጠቅላዩን ማብራሪያ በማድመጥ ላይ፤

በዚያ ኢኮኖሚ ተኮር ማብራሪያቸው ቁጥሮችን ሲጠቅሱ የተደመጡት ጠቅላዩ፣ በግብርናው ዘርፍ በ2017 ዓ.ም. 7 ነጥብ 3 በመቶ ዕድገት መመዝገቡን እና ይኽም ከጥቅል ዓመታዊ ዕድገቱ የ2 ነጥብ 3 ድርሻ እንዳለው አመልክተዋል። ከለውጡ በኋላ ከፍተኛ ለውጥ እና ዕድገት ተመዝግቦበታል ላሉት የግብርናው ዘርፍ ቁጥራዊ መረጃዎችን ሲያጣቅሱም፤ በ2010 ዓ.ም. የስንዴ ምርት 47 ሚሊዮን ኩንታል ይመረት እንደነበር አንስተው፣ በ2017 ዓ.ም. ከ280 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ ማምረት መቻሉ ትልቅ ለውጥ እንደሆነ ተናግረዋል። እርሳቸው ወደ ምክር ቤቱ አዳራሽ ከመምጣታቸው ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ፣ አገሪቷ የውጭ ዕዳዎቿን መክፈል ስለመቻል/ አለመቻሏ ሲዘገብ በነበረው ርዕሰ-ጉዳይ ላይም የተናገሩት የገዢው ፓርቲ ፕሬዝደንት፤ ኢትዮጵያ ከዓለም ዓቀፍ አበዳሪዎች ያለባት ዕዳ ከ23 ቢሊዮን ዶላር እንደማይበልጥ አንስተው፣ አገሪቱ አሁን ያለባትን ዕዳ ለማስተዳደር ብሎም ለመክፈል ችግር የለባትም ሲሉም፣ እንደራሴዎቹን አያሳስባችኹ ብለዋቸዋል። በ2018 በጀት ዓመት የሚኖረው የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ከ2017 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር በኹለት ዕጥፍ እንደሚያድግም ጠበቅ አድርገው ሲናገሩ ተደምጠዋል። በዚኹ ርዕሰ-ጉዳይ ዙሪያ ከተነሱላቸው ጥያቄዎች አንዱ በነበረው የዋጋ ንረት ጉዳይም ሲናገሩ፣ የኑሮ ውድነት እና የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት 440 ቢሊዮን ብር ድጎማ መደረጉን አስታውሰው፣ የጥቅምት ወር የዋጋ ንረት ወደ 11.7 በመቶ መውረዱን ሲናገሩ ተደምጠዋል።

በያዝነው ዓመት የመጀመሪያ በሆነው በዚኽ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ውሏቸው፣ ስለ ኮሪደር ልማቱ እና መንግስታቸው አብዝቶ ስለሚተገብረው የአረንጓዴ አሻራም የተናገሩት ዶ.ር. ዐቢይ፤ የኮሪደር ልማት ሥራው ከፍተኛ የአመለካከት ለውጥ የመጣበት ሥራ መሆኑን ገልጸዋል። ሰው ልማዱን ለማስቀረት ቢቸገርም በሂደት አዲሱን ዓለም እንደሚቀበል ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የኮሪደር ልማት ሥራችን ከፍተኛ የፈጠራ ዐቅም እና የኑሮ ዘዬ ለውጥ እያመጣ ነው ሲሉም ተናግረዋል። የኮሪደር ልማት ሥራው ብዙ ዐቅሞች እንዲወጡ ማስቻሉንም አንስተው፣ ከወንዝ ዳርቻዎች ልማት ጋር በተያያዘ የውጭ ሰዎች ከብዷቸው የተዉትን የአገራችን ሰዎች በብቃት እየሠሩት ነው ሲሉም ተሰምተዋል። በአረንጓዴ አሻራ ዙሪያም ሲያወሱ፣ ኢትዮጵያ ለዓለም የአየር ንብረት ለውጥ 48 ቢሊዮን ዶላር ፈሰስ አድርጋለች ያሉት ዶ.ር. ዐቢይ፣ ይኽም በዕርዳታ እና በድጋፍ ቢሆን የማይታሰብ ነበር ብለዋል።

## የባሕር በሩ ጉዳይ. . .

የኢፌዴሪው ፕሬዝደንት የተከበሩ ታዬ አጽቀሥላሴ፣ መስከረም 26 2018 ዓ.ም. ለየሕዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች የጋራ ስብሰባ ያደረጉትን የመክፈቻ ንግግር አስመልክቶ ከእንደራሴዎቹ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ፣ ሰንበት ስላለው የኢትዮጵያ የባሕር በር በኩር ጥያቄ፣ እንደኹልጊዜውም ጠበቅ ያሉ የመንግስታቸውን አቋሞች አብራርተዋል። ከቀይ ባሕር እና የባሕር በር ጋር በተያያዘ ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት የጀመሩት የብሔራዊ ጥቅም ጉዳይን በማንሳት ሲሆን፤ ኹሉም አገር መጠኑ ይነስም ይብዛ፣ ሀብቱ ይብዛ ይነስም የተፈጥሮ ጸጋውን ሌላውን ሳይጎዳ የመጠቀም መብት አለው ያሉት ዶ.ር. ዐቢይ፣ ተፈጥሮ ያደለችውን ሀብት በሌላ ላይ ጉዳት ሳያመጣ መጠቀም የሁሉም አገር መብት ነው ሲሉ ሰፋ ወዳለው ማብራሪያቸው ዘልቀዋል።

ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን በሚመለከት ኢ-ርዕታዊ፣ ኢ-ፍትሓዊ እና የበደል የመጨረሻው በደል የተፈጸመባት አገር ነች ሲሉ የተደመጡት ርዕሰ-መንግሥቱ፣ ኢ-ፍትሓዊ እና ኢ-ርዕታዊ ውሳኔ ባለበት ኹኔታ የተሟላ ሰላም ሊፈጠር እንደማይችል አስገንዝበዋል። የቀይ ባህር ጉዳይ ሕጋዊ፣ ታሪካዊ፣ መልካ ምድራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄ ነው ብለን እናምናለን ያሉት የአገሪቷ ጠቅላይ ጦር አዛዥ፣ “ይሄ ጥያቄ አንዳንዱ ነገ ካልተመለሰ ይላል፤ አንዳንዱ ነገ እኔ ስመጣ ካልጀመርኩት ይላል፤ ኹለቱም አያስፈልግም” ብለዋል። “ጦርነት የለም ማለት የተኩስ ድምጽ አይሰማም ማለት አይደለም፤ እውነተኛ ፍትሕ ካልተረጋገጠ በማንኛውም ሰዐት ጦርነት ሊፈጠር ይችላል” ሲሉም አክለዋል። ቀይ ባሕርን ስለማጣት እና ዳግም ስለማግኘት ሲያነሱም፣ “ቀይ ባሕርን ኢትዮጵያ ለማጣት 30 ዓመት እና ከዚያ በላይ የወሰደ ትግል ነበር፤ በ30 ዓመት ትግል ውስጥ በብዙዎች ርብርብ ነው ኢትዮጵያ ቀይ ባሕርን ያጣችው” ያሉት ዶ.ር. ዐቢይ፤ “ዳግም ለማግኘት በተረጋጋ መንገድ፣ በሰከነ መንገድ፣ በውይይት መሄድ አስፈላጊ ነው፤ የፈለገ ብንወያይ ግን ለማጣት የፈጀብንን 30 ዓመት ለማግኘት ይፈጅብናል ብዬ ግን አላስብም፤ ግዜው ግን በቂ ስለሆነ በተረጋጋ መንገድ ማየት ያስፈልጋል።” ሲሉ ተደምጠዋል።

“አንዳንዱ ዛሬን ብቻ ስለሚያስብ ዳራውን ልስጥ” ሲሉ ወደ ኋላ መለስ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ “በመጀመሪያ ኢትዮጵያን ቀይ ባሕርን ያሳጣትን ውሳኔ ማን ወሰነው? ካቢኔው ይሆናል ብለን የካቢኔ ዶክመንት ብናገላብጥ የለም፤ ካቢኔ አያውቀውም፤ አይ ምክር ቤት ይሆናል የወሰነው ብለን ብናስብ ምክር ቤቱም አልነበረ፤ ውሳኔውን ምክር ቤት አያውቀውም፤ የለም የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕዝበ-ውሳኔ ወስኖ እንዳይሆን እንዳይባል ነበርን እኛም ያኔ” በሚል የጊዜ ምጣኔውን ያስቀምጡት ጠቅላዩ፤ “የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልወሰነው፣ ተወካዮቹ ያላዩት፣ ቢያንስ ቢያንስ አሥፈጻሚ ካቢኔ ያላየውን ውሳኔ ማን ወሰነው? ማጣትን የሚያክል ነገር ያጣንበት መንገድ የሕጋዊነት ችግር እንዳለበት ማሳያው ተቋሞች አልገቡበትም፤ ካቢኔ አያውቀውም፤ አንድ ገጽ ወረቀት ማግኘት አልቻልንም እንዴት እንዳጣነው የሚያስረዳ” ሲሉም ለእንደራሴዎቹ ሂደቱን አጠር አድርገው አስረድተዋል፤ “ማን ወሰነው? ይሄ ነው ጥያቄው” ሲሉም መጥይቂያዊ ቃላትን ጠበቅ አድርገው ሰንዝረዋል።

በዚኽ የባሕር በር እና ተያያዥ ጥያቄዎች ዙሪያ፣ መንግስታቸው ለሰላም እና ለንግግር ቅድሚያ እንደሚሰጥ በተደጋጋሚ ሲናገሩ የተደመጡት ጠቅላይ ጦር አዛዡ ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ፣ ይኽንን ሐሳባቸውንም በዚያ የዕለተ-ኀሙስ ውሏቸውም ደግመውታል። ኢትዮጵያ ቅድሚያ የምትሰጠው ለሰላም” እና ንግግር” መሆኑን ያስረዱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ፣ አገሪቱ ቀይ ባሕርን መጠቀሟ አይቀሬ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ እንዲያሸማግሏቸው ለበርካታ አገራት ጥያቄ ማቅረባቸውንም ተናግረዋል። የሽምግልና እና የመፍትሔ ሐሳብ አምጡልን ጥያቄ ከቀረበላቸው አገራት መካከል አሜሪካ፣ ቻይና እና ሩሲያ እንደሚገኙበትም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቁመዋል። “አሁን ለተከበረው ምክር ቤት መግለፅ የምፈልገው ነገር የኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ማግኘት ጉዳይ አይቀሬ ስለሆነ ቅድሚያ የምንሰጠውም ለሰላም እና ንግግር ስለሆነ፣ አባካችሁ ሽምግሉን እና መፍትሔ አምጡልን፤ ይሄው ነው ጥያቄያችን” ሲሉም ተደምጠዋል። “ሆኖም” አሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ “ሆኖም፣ እንሸመግላችኋለን፤ ሰላም ያስፈልጋል እያሉ ማዘናጋት ከሆነ ግን ብዙ የሚሄድ አይመስለኝም ጉዳዩ” ሲሉ አክለዋል። በዚኹ የንግግራቸው አውድ ውስጥ ኤርትራንም ያነሱት ጠቅላዩ፣ “የኤርትራ ሕዝብ አሁንም ወንድም ሕዝብ ነው፤ ምስኪን ሕዝብ ነው፤ አገሩን ለቆ እየተሰደደ ያለ ሕዝብ ነው፤ ፍላጎታችን ከዚኽ ሕዝብ ጋር መተባበር ነው” ሲሉ ገልፀው፤ “በፍፁም የውጊያ መሻት የለንም” ሲሉም ከዚኽ ቀደም በዚያው ምክር ቤት ያነሱትን ሐሳብ ጠብቅ አድርገው ደግመውታል። የውጊያ ምናልባትነትንም ሲያነሱ፣ ውጊያ ቢቀሰቀስ እንደ ከዚኽ ቀደሙ ጊዜያት አጋዥ አገራት እና ኃይሎች እንደማይኖሩ አበክረው አሳስበዋል። “አሁን ውጊያ እንትና ያግዘኛል፣ እንትና የሚባል ነገር የለም፤ ሰው እንዴት ዩክሬንን እያየ፣ ፍልስጤምን እያየ ስለማገዝ ያወራል? ማንም አይሞትልህም፤ ሞራል ይሰጥኻል እንጂ አይሞትልህም፤ መጨረሻ የምትሞተው አንተ ነህ፤ አያዋጣም” ሲሉም አበክረው ተናግረዋል።



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ እና
አፈ-ጉባኤው ታገሰ ጫፎ በማብራሪያው ዕለት፤

# የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባሮች



የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ምንም እንኳን በወርኃ ጥቅምት ሕግጋት ባያወጣ እና ረቂቅ ሕግጋትንም ወደ ሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ባይመራም፣ የሕግ የማውጣት ተግባር ሂደት አካል የሆኑ ኹለት አስረጂ መድረኮችን አካሂዷል። እነዚኽም፣ የዕፅዋት ጥበቃ እና ኳራንቲን ረቂቅ እና የግብርና ኤክስቴሽን አገልግሎት እና አሠተዳደር ረቂቅ ዐዋጆችን የተመለከቱ ነበሩ።

## አስረጂ መድረኮች

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በወርኃ ጥቅምት በቀዳሚነት ያካሄደው የአስረጂ መድረክ፣ **በዕፅዋት ጥበቃ እና ኳራንቲን ረቂቅ ዐዋጅ** ዙሪያ ያካሄደው ነበር። መድረኩን ያዘጋጀው በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፣ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ሰሎሞን ላሌ፣ ኢትዮጵያ በብርቅዬ ብዝኀ ሕይወት የታደለች ብትሆንም፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመጣው ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ክስተት፣ በተለይም በተባይ አማካኝነት ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል። ነባሩ የሕግ ማዕቀፍ ለረጅም ጊዜ የቆየ፣ በምርምር ያልተደገፈ እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ያላካተተ በመሆኑ፣ ዓለም ዓቀፍ የዕፅዋት ጥበቃ ስምምነቶችን የተከተለ አዲስ ዐዋጅ ማውጣት የግድ መሆኑን ሰብሳቢው ማስረዳታቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ያሳያል። የረቂቅ ዐዋጁን ዝርዝር ማብራሪያ ያቀረቡት የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን አማካሪ አቶ ተክሉ ባይሳ በበኩላቸው፣ ነባሩ ረቂቅ ዐዋጅ ወቅታዊ እና ዝርዝር ጉዳዮችን ያላካተተ መሆኑን ጠቁመው፣ በዚህ ምክንያትም አግባብነት ያለው የተባይ ሥጋት ትንተና ለማድረግ እና በመግቢያ በሮች ቁጥጥር ለማድረግ ባለመቻሉ ጉዳት እየደረሰ መሆኑን አንስተዋል ተብሏል። በዚያው ዕለት እና በዚኹ ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያ ከአስረጅዎች ጋር በተካሄደ ሌላ መድረክ ላይ የተገኙት የተከበሩ አቶ ሰሎሞን፣ ቅድመ ምርት እና ድኅረ-ምርትን ከተባይ ለመጠበቅ እንዲቻል ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችን ያስጠበቀ እና ጊዜውን የዋጀ ሆኖ የተዘጋጀ መሆኑን ሲናገሩ ተደምጠዋል። በግብርና ሚኒስቴር የእርሻ እና ሆልቲካልቸር ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. መለሰ መኮንን በበኩላቸው፣ ቀደም ሲል የወጡት ድንጋጌ ቁጥር 56/1963 እና ደንብ ቁጥር 4/1985 ለረጅም ጊዜ ያገለገሉ በመሆኑ፣ ዓለም ዓቀፍ ሥምምነቶች፣ ደረጃዎች፣ ሕጎች እና አሠራሮች ከጊዜ ወደጊዜ በፍጥነት እየተሻሻሉ እና እየተለወጡ መምጣታቸውን ተከትሎ፣ በአገራችንም የዘርፉን ማነቆ ለመፍታት የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት፣ ዘመኑን የዋጁ የአሠራር ሥርዓታትን መዘርጋት እና መተግበር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ብለዋል ተብሏል።

በዚኹ ጥቅምት ወር ላይ የተካሄደው ኹለተኛው የአስረጂ መድረክ፣ **የግብርና ኤክስቴሽን አገልግሎት እና አሠተዳደር ረቂቅ ዐዋጅን** የተመለከተው ሲሆን፣ መድረኩን ያዘጋጀው በእንደራሴዎች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር ተብሏል። በመድረኩ ላይ የተገኙት፣ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ሰሎሞን ላሌ፣ መንግሥት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በትኩረት እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ በዘርፉ ምርት እና ምርታማነትን ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና ያለውን የአፈር ማዳበሪያ ፋብሪካ ለመገንባት የመሠረት ድንጋይ መጣሉንም አውስተዋል። በግብርና ሚኒስቴር የእርሻ እና ሆልቲካልቸር ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታው ዶ.ር. መለሰ መኮንን፣ ረቂቅ ዐዋጁ ከፖሊሲ እና ከስትራቴጂው በመነሳት ከሌሎች አገራት ተሞክሮ በመውሰድ እና ከነባራዊ ኹኔታ ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ እንደተዘጋጀ መናገራቸውን ዘገባው ጠቅሷቸዋል። በዚኹ ዐዋጅ ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ከቀናት በኋላ በተካሄደ ይፋዊ የውይይት መድረክ ላይ የታደሙት ሰብሳቢው የተከበሩ ሰሎሞን ላሌ፣ ረቂቅ ዐዋጁ የግብርና ክፍለ-ኢኮኖሚውን በብዙ መልኩ የሚቀይር መሆኑን ጠቅሰው፣ ረቂቁ በኢትዮጵያ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ አሠተዳደር እና ልማት እንዲኹም በተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ ያለውን የተደራሽነት፣ የጥራት፣ የዐቅም እና የአፈጻጸም ውስንነትን ለመቅረፍ የሚያስችል እንደሆነ መናገራቸውን ዘገባው የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷል።



አስረጂ መድረኩ በከፊል

# የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደራሴዎች፣ ከዋና ዋና ሥራዎቻቸው አንዱ የሆነው የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ሲሆን፤ በዚኽ ረገድም፣ በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ ጥቅምት የተለያዩ ተቋማትን ሪፖርቶች አድምጠዋል፤ ከምክር ቤቱ ወጣ ብለውም የተለያዩ ተቋማትን በ'የኮሚቴዎቻቸው አማካኝነት በአካል ሲመለከቱ፣ በዛ ያሉ የመስክ ጉብኝቶችንም ከውነዋል።

## የተቋማት ሪፖርቶች

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በዚኽ ሽፋን በሰጠነው ጥቅምት ወር፣ የኹለት ተቋማትን የ2018 ዓ.ም. የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም መገምገሙን የምክር ቤቱ መረጃዎች ይጠቁማሉ። የመጀመሪያው የፌደራል ተቋም **ፍትሕ ሚኒስቴር** ሲሆን፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የዚኹ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤትን እና የተጠሪ ተቋማቱን የሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀምን ሲገመገም፣ ሪፖርቱን ያቀረቡት የፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. ኤርሚያስ የማነ ብርሃን ነበሩ። ሚኒስትር ዴኤታውም፣ የሕግ ጥናት ማርቀቅ እና አፈጻጸሙን የማሻሻል፣ የጥብቅና አሥተዳደር እና ክትትል የማሳደግ፣ የመንግሥት እና የሕዝብን ፍትሐ-ብሔራዊ ጥቅም የማስጠበቅ እንዲኹም የአሥተዳደር ፍትሕ እና የፌዴራል ሕጎች ተፈፃሚነት የማሳደግ ሥራ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰዋል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ እፀገነት መንግስቱ፣ የፍትሕ አገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመቅረፍ እንዲያስችል ከተለያዩ ሕግ አሥፈጻሚ እና ባለድርሻ ተቋማት ጋር እየተደረጉ የሚገኙ ቅንጅታዊ አሰራሮች ተጠናክረው መቀጠል ይገባቸዋል ብለዋል ተብሏል። የበርካታ ዜጎችን ሕይወት እየቀጠፈ የሚገኘውን ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ለመግታት የኹሉም ኅብረተሰብ የተቀናጀ ድጋፍ ያስፈልጋል ያሉት ሰብሳቢዋ፣ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች እና ኤጀንሲዎች ለሕግ በማቅረብ የሕግ ተጠያቂነትን ማስፈን እንዲኹም የሕዝቡን አመኔታ መጨመር ያስፈልጋል ሲሉ መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያሳያል። ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ኢሳ ቦሩ በበኩላቸው፣ የፍትሕ ተቋማት በቀጣይ ለሚደረገው አገራዊ ምርጫ የሲቪል ማኅበራትን ተሳትፎ ለማሳደግ እንዲቻል የሚያግዙ መደላድሎችን መፍጠር ይገባቸዋል ሲሉ በአጽዕኖት ተናግረዋል። በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ተስፋዬ ዳባ በበኩላቸው፣ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር የተሰማሩ አካላትን ተከታትሎ በሕግ እንዲጠየቁ ከማድረግ አኳያ ከተለያዩ የሕግ አሥፈጻሚ እና ዓለማ ዓቀፍ ተቋማት ጋር በትብብር እየተሰራ መሆኑን አንስተዋል ሲል ዘገባው ጠቅሷል።



የፍትሕ ሚኒስቴር የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በከፊል



የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አሥተዳደር ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ ትዕግሥት ሃሚድ

በወርኃ ጥቅምት ተረኛ የሩብ ዓመቱ የአፈጻጸም ሪፖርት አቅራቢ የነበረው፣ **የኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አሥተዳደር** ነበር። የአሥተዳደሩ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ ትዕግሥት ሃሚድ፣ በተለያዩ ተቋማት መሠረተ ልማቶች ላይ 13,443 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች መደረጋቸውን ጠቅሰው፣ ተቋማቸው የሳይበር ጥቃትን የመከላከል ዐቅሙን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻለ በመምጣቱ፣ ሪፖርታቸው በሸፈነው የጊዜ ምጣኔም የመከላከል ዐቅሙ 97.8 በመቶ መድረሱን ተናግረዋል ተብሏል። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ፣ በተለያዩ ተቋማት ይኽን ያህል ቁጥር ያላቸው የሳይቨር ጥቃት ሙከራዎች ተደርገው 97.8 በመቶ የመከላከል ጥረት በጥንካሬ የሚወሰድ መሆኑን ጠቁመው፣ ተቋሙ የመከላከል ዐቅሙን ከ99 በመቶ በላይ ከፍ ለማድረግ በትኩረት መሥራት እንደሚጠበቅበት መናገራቸውን መረጃው ጠቅሷቸዋል። ምክትል ሰብሳቢው አክለውም፣ ኹሉም ተቋማት ኢንተርኔትን ስለሚጠቀሙ የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አሥተዳደር ከተለያዩ ተቋማት በትብብር በመሥራት፣ ሜጋ ፕሮጀክቶችን እና የፋይናንስ ተቋማትን ከሳይበር ጥቃት መከላለከል እንዳለበትም አስገንዝበዋል።

## የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ወርኃ ጥቅምትን ያጠናቀቀው የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድን ማብራሪያዎች በማድመጥ እና የተቋማቱን ሪፖርቶች በማድመጥ ብቻም ሳይሆን፣ በዛ ያሉ ተቋማትን በተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎቹ በኩል ሲጎበኝ፣ ቁጥራቸው በዛ ያሉ የመስክ ጉብኝቶችንም አድርጓል።

## የተቋማቱ ጉብኝቶች

እንደራሴዎቹ፣ በወርኃ ሰኔ ከጎበኟቸው ተቋማት መካከል በቀዳሚነት ማሳያ የሚሆነው **የኢትዮ- ኢንጂነሪንግ ግሩፕ** ሲሆን፣ ጎብኚው ቋሚ ኮሚቴም በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ልማት ድርጅት ቋሚ ኮሚቴ ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና፣ ኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ተልዕኮውን እና ራዕዩን ለማሳካት የሠራተኛው እና የአመራሩ ቁርጠኝነት ሚናቸው የጎላ መሆኑን አስገንዝበዋል ተብሏል። ሰብሳቢው አክለውም፣ ለአገር ያለውን ፋይዳ በመረዳት ተቋሙን ወደትውልድ ለማስተላለፍ ሠራተኛው በባለቤትነት ስሜት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንዳለበት አሳስበዋል፡፡ የቋሚ ኮሚቴው አባላት በበኩላቸው፣ ተቋሙ ማኅበራዊ ኃላፊነትን ከማወጣት እና አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለመደገፍ እያደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አመላክተዋል ተብሏል። የተቋሙ ዋና ሥራ አሥፈፃሚ ኮሎኔል ሽጋው ሙሉጌታ በተራቸው፣ ተቋማቸው በርካታ ውስብስብ ችግሮች ቢኖሩበትም ፈተናዎችን ተቋቁሞ አምራች ኢንዱስትሪዎች በሙሉ ዐቅማቸው እንዲያመርቱ እና የላቀ ውጤት ማስመዝገብ እንዲችሉ በትኩረት እየተሰራ እንደሆነ መግለፃቸውን ዘገባው ያሳያል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ስለሽ ኮሬም፣ ተቋሙ ራዕዩን ከግብ ለማድረስ በምሥራቅ አፍሪካ ጥራት ያላቸውን ምርቶች በማምረት ደንበኛን በማርካት እና ተወዳዳሪ በመሆን የውስጥ የገቢ ዐቅምን ማሳደግ እንደሚገባ መናገራቸው ተጠቅሷል።



የመንግስት ልማት ድርጅት ቋሚ ኮሚቴ የኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕን በጎበኘበት ወቅት

ሌላይኛው የወሩ ተጎብኚ ተቋም፣ **የትምህርት ፈተና እና ምዘናዎች አገልግሎት** ሲሆን፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉብኝቱን ማከናወኑን ከምክር ቤቱ የወጣው ዘገባ ያሳያል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፣ ተቋሙ ትልልቅ አገራዊ ሥራዎችን ሲሰራ እንደነበረ ገልፀው፣ ትውልዱ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የሚያልፍበት የትምህርት ግምገማ፣ ምዘና እና ፈተና በተቋሙ ስለሚሰጡ ኃላፊነቱ ቀላል እንዳልሆነ ጠቁመዋል። ሰብሳቢው አክለውም፣ የ12ኛ ክፍልን አገራዊ ፈተና የሚወስዱ ተማሪዎች፣ በተለያዩ ነባራዊ ኹኔታ ውስጥ ሆነው ስለሚፈተኑ የፈተና ዝግጅቱ አካታች እና ፍትሓዊ እንዲሆን በቀጣይ ሊሰራበት እንደሚገባም ማሳሰባቸው ተሰምቷል። ምክትል ሰብሳቢዋ የተከበሩ ዶ.ር. ቤተልሔም ላቀው በበኩላቸው፣ ተቋሙ በወረቀት የነበሩትን መረጃዎች በዲጂታል ሥርዓት ውስጥ በአንድ ማስቀመጡ እና አዳዲስ አሠራሮች ተግባራዊ መደረጋቸው የሚበረታታ መሆኑን ገልፀዋል ተብሏል።

## የመስክ ጉብኝቶች

በዚኽ ዕትም በሸፈነነው ጥቅምት ወር፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ካደረጋቸው የመስክ ጉብኝቶች መካከል በቀን ምጣኔ በቀዳሚነት ለማሳያነት የምትነሳው **ድሬ ዳዋ** ስትሆን፣ ጎብኚውም፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እንደነበር መረጃው ይጠቅሳል። በድሬዳዋ አሥተዳደር እየተከናወኑ የሚገኙ መሠረተ ልማቶችን እና የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን ተዘዋውረው የተመለከቱት የኮሚቴው አባላት፣ በከተማዋ የሕዝቡን የልማት ጥያቄዎች ለመመለስ እና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመፍታት እየተከናወኑ የሚገኙት አበረታች ሥራዎች መጠናከር እንዳለባቸው መናገራቸው ተዘግቧል። ይሁንና፣ ከተማዋን የኮንፈረንስ መዳረሻ ለማድረግ በ2.3 ቢሊየን ብር በጀት እየተሰራ ያለው የኮንቬክሽን ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት፣ በታቀደለት ጊዜ እና በጀት ልክ እየተፈጸመ እንዳልሆነ ቋሚ ኮሚቴው አስታውቋል ተብሏል። እንደ ምክር ቤቱ መረጃም ከሆነ፣ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ፕሮፌሰር መሐመድ አብዶ፣ በድሬ ዳዋ እየተገነቡ የሚገኙ መሠረተ ልማቶች የነዋሪውን የልማት እና የአገልግሎት ጥያቄዎች በፍጥነት እና በጥራት እንዲመለሱ የሚያግዙ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎን ጨምሮ፣ ከፍተኛ የምክር ቤቱ ሰዎች **በቦሌ ለሚ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን** ያደረጉት የመስክ ጉብኝትም አንዱ የወሩ ዓይነተኛ ክንውን ነበር። የኢንዱስትሪ ፓርኮች የልማት ዘላቂነትን ለማረጋገጥ የማይተካ ሚና እንዳላቸው በወቅቱ የተናገሩት አፈ-ጉባኤው ታገሰ ጫፎ፣ ፓርኮቹ የአገርን ልማት በዘላቂነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሬ እያስገኙ መሆኑን እና በአገር ውስጥ ዐቅም በማምረት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በመተካት ረገድም ትልቅ ድርሻ እየተወጡ መሆናቸውን መናገራቸውን የምክር ቤታቸው መረጃ ጠቅሷቸዋል። ፓርኮቹ ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው እንዲሰሩ በመሠረተ ልማት እና በኃይል አቅርቦት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ምክር ቤቱ ከጎናቸው እንደሆነም የተከበሩ አቶ ታገሠ ተናግረዋል። ይኽንኑ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን የጎበኙት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ በበኩላቸው፣ ከጥቅል አገራዊ ምርት ውስጥ 44 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ለመሸፈን ጥረት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል።



የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አመራሮችና አባላት በቦሌ ለሚ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን እና በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ምልከታ ላይ

አፈ-ጉባኤዋ አክለውም፣ ብረትን ጨምሮ እንደ መስታወት ያሉ ከዚኽ ቀደም በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ወደ አገር ቤት ይገቡ የነበሩ ምርቶች የአገር ውስጥ ጥሬ እቃን በመጠቀም የአካባቢ ደኅንነትን በጠበቀ ኹኔታ በአገር ውስጥ ለማምረት እየተሰሩ ያሉት ሥራዎች አበረታች መሆናቸውን ጠቁመዋል ተብሏል።



የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በጋምቤላ የመስክ ጉብኝት ወቅት

ጥቅምት 21 2018 ዓ.ም. ወደ **ደቡብ ኢትዮጵያ** ወላይታ የተጓዙት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ በከተማው የመብራት አገልግሎት ማዕከል ላይ የመስክ ምልከታ ሲያደርጉ፤ በጉብኝታቸው ወቅትም፣ የማዕከሉ የ2017 ዓ.ም. በጀት ዓመት እና የ2018 ዓ.ም. የሩብ ዓመት ሪፖርት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው አባል እና የመስክ ምልከታው ቡድን መሪ የተከበሩ ዶ.ር. ዘውዱ ታደሰ፣ የተቋሙን ክፍተቶች ከመሙላት አንፃር ወደ መሬት አውርዶ መሥራት እንደሚያስፈልግ አሳስበው፣ የትራንስፖርት እጥረት የሠራተኛውንም ሆነ የደንበኞችን እርካታ የሚጎዳ በመሆኑ መፍታት የሚቻልበት ኹኔታ ቢፈጠር ብለዋል ተብሏል። እነዚኹ የቋሚ ኮሚቴው አባላት፣ በዚያው ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የሚገኘውን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዲላ ዲስትሪክትን መጎብኘቱን ከመስክ ምልክታው የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ይኽንንም የኮሚቴውን ቡድን የመሩት የተከበሩ ዶ.ር. ዘውዱ ታደሰ ሲሆኑ፣ እርሳቸውም ዲስትሪክቱ ካለው ስፋት አንፃር 43 ቅርንጫፎች በቂ ባለመሆናቸው ያለውን ተደራሽነት ለማስፋት በትኩረት መሥራት አለበት ብለዋል ተብሏል። ከእነዚኽ ኹለት ጉብኝት በተጨማሪም፣ በዚያው ክልል የሚገኘውን የኢትዮ-ቴሌኮምን ዲላ ማዕከል የተመለከቱት እንደራሴዎቹ፣ ማዕከሉ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እየከወነ እንደሆነ መመልከታቸውን ገልፀው፣ በ'የማዕከላቱ የሕጻናት ማቆያ ሊኖር ይገባል ሲሉ በቡድን መሪያቸው የተከበሩ ዘውዱ ታደሰ በኩል አስተያየታቸውን መሰንዘራቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

በዚኹ ወርኃ ጥቅምት በእንደራሴዎቹ በመጎብኘት ለማሳያነት ልንጠቅሳት የምትችለው ድንበርተኛዋ ክልል **ጋምቤላ** ስትሆን፤ የመስክ ምልከታውም የተካሄደው በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኩል ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ቡድን አስተባባሪ የተከበሩ ወይዘሮ ለጢፋ አባ ተማም፣ ቋሚ ኮሚቴው መንግስት የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ እያከናወነ ያለውን ሥራ እና የሕዝቡን ተጠቃሚነት በተጨባጭ በመመልከት ላይ ይገኛል ብለዋል ተብሏል። የጋምቤላ ክልል የእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ልማት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊው ዶክተር ሞክ ያንግ በበኩላቸው፣ በክልሉ እስከ አኹን በርካታ ወጣቶች በተለያዩ የልማት ሥራዎች ተጠቃሚ እየሆኑ መምጣታቸው መጥቀሳቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል። እንደራሴዋ የተከበሩ ወ/ሮ ለጢፋ፣ ወደ ክልሉ የአቦቦ መንገሽ እና የጎደሬ ወረዳዎችም የመስክ ጉብኝት ማድረጋቸው ተዘግቧል። በዚያ ጉብኝታቸውም፣ በክልሉ እየተካሄደ ያለው የማዕድን ቁፋሮም ሆነ የቡና ልማቱ ደኑን በማይጎዳ መልኩ መሰራት እንዳለበት አመላክተዋል ተብሏል።

ጥቅምት 25 ቀን በዋና ከተማዋ **አዲስ አበባ** ወደሚገኘው የዕዳ እና የሀብት አሥተዳደር ኮርፖሬሽን የደረሱት በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ልማት ድርጅቶች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ በቡድኑ መሪ የተከበሩ ወ/ሮ አዲስ አለማየሁ አማካኝነት፣ ኮርፖሬሽኑ ዕቅዱን በአግባቡ በማቀድ እና ግቡን በግልጽ በማስቀመጥ የሪፎርም ሥራውን በቅንጅት መሥራት እንዳለበት ገልጸዋል ተብሏል። በኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እና ኮርፖሬት ሰርቪስ መምሪያ ሥራ አሥፈጻሚው አቶ ለእውነት ካሳሁን፣ የተቋማቸውን የ2018 ዓ.ም. ዕቅድ እና የሩብ ዓመት የሥራ አፈጻጸም ባቀረቡበት ወቅት፣ በሩብ ዓመቱ 19.72 ሚሊዮን ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 9.72 ሚሊዮን ብር መገኘቱን በዚያ ላገኟቸው እንደራሴዎች ነግረዋቸዋል ተብሏል። ከዚኽ በተጨማሪም የኮርፖሬሽኑ የሰው ሀብት አሥተዳደር መመሪያ ጸድቆ ተግባራዊ ባለመሆኑ፣ የሰው ሀብት አሥተዳደር እና ቅጥር ላይ ተፅዕኖ እያስከተለ መሆኑንም እንደችግር አክለው ማንሳታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቁሟል።

ጥቅምት መገባደጃ ላይ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መጎብኘቷ የተዘገበው **ደቡብ ምዕራብ** ክልል ውስጥ የምትገኘው ቤንች ሸኮ ዞን መሆኑ ሲዘገብ፤ ኮሚቴውም፣ በክልሉ በደረሰ የመሬት መንሸራተት አደጋ የተፈናቀሉ ዜጎችን ተዘዋውሮ ጎብኝቷል። የቋሚ ኮሚቴው አባል እና የመስክ ምልከታው ቡድን መሪ የተከበሩ አቶ ሳዲቅ አደም፣ በተከሰተው አደጋ የተፈናቀሉ ዜጎች ጊዜያዊ መጠለያ እንዲያገኙ ከማድረግ ባሻገር ጤና፣ ትምህርት፣ ምግብ እና ሌሎች ድጋፎች በመደረጉ ከወረዳ እስከ ክልል የተሰሩ ሥራዎች አበረታች መሆናቸውን ጠቁመዋል ተብሏል። ሌሎቹ ቋሚ ኮሚቴው አባላት በበኩላቸው፣ አሁንም በአደጋ ስጋት ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ቀበሌዎችን በመለየት አደጋው ከመፈጠሩ በፊት ለነዋሪዎቹ መጠለያ ቦታ አዘጋጅቶ ማስፈር እንደሚገባ ማመላከታቸውን ከመስክ ምልክታው የተገኘው ዘገባ ይጠቁማል።

በዚኽች ዘጠነኛ የእንደራሴ ዕትም ሽፋን በሰጠነው የመስክ ጉብኝት ከተከናወኑባቸው አካባቢዎች አንዷ **ሲዳማ ክልል** ስትሆን፣ ጉብኝቱን የከወኑትም በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ነበሩ። ቋሚ ኮሚቴው፣ በሀዋሳ ከተማ ደብሊው ኤም ኢንጂነሪንግ፣ የሴራሚክ ማምረቻ እና አለም ግራናይት እና ማርብል ፋብሪካን ተዘዋውሮ የመስክ ምልከታ አድርጓል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው አባል እና የምልከታ ቡድኑ መሪ የተከበሩ ዶ.ር. ዘውዱ ታደሰ ይኽ ለአገር ልማት ወደፊት የተሻለ ቦታ ለመገኘት ትልቅ ሚና ያለው ፋብሪካ በመሆኑ በትጋት መሥራት ይገባል ብለዋል ተብሏል።

# የእንደራሴዎቹ የውክልና ሥራ

የኢፌዲሪ እንደራሴዎች፣ ከሐምሌ ወር እስከ መስከረም ወር መጨረሻ ሳምንት ድረስ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ዋናው የውክልና ሥራ መሆኑ ይታወቃል። ያም ሆኖ፣ በወርኃ ጥቅምት ኹለት እንደራሴዎች ወደ 'ምርጫ ወረዳዎቻቸው በመሄድ የወከሏቸውን የማወያየት እና ጥያቄዎቻቸውን የመስማት ተግባራቸውን ከውነዋል።

የኢፌዲሪ እንደራሴዎች፣ ከሐምሌ ወር እስከ መስከረም ወር መጨረሻ ሳምንት ድረስ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ዋናው የውክልና ሥራ መሆኑ ይታወቃል። ያም ሆኖ፣ በወርኃ ጥቅምት ኹለት እንደራሴዎች ወደ 'ምርጫ ወረዳዎቻቸው በመሄድ የወከሏቸውን የማወያየት እና ጥያቄዎቻቸውን የመስማት ተግባራቸውን ከውነዋል።

በጥቅምት የመጀመሪያው ሳምንት መገባደጃ ላይ ወደ ኢትዮጵያ **ሶማሌ ክልል** ፋፈን ዞን ሐረዋ ወረዳ የደረሱት የተከበሩ ከማል ሃሺ መሐሙድ ከመራጮቻቸው ጋር ተወያይተዋል። በውይይቱም የወረዳው የመንግሥት ሠራተኞች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች እና የሃይማኖት አባቶች ሲሳተፉ፣ በወረዳው እየጎለበተ የመጣውን ልማት ለማስቀጠል በሚቻልባቸው መንገዶች ከተወያዮቹ ጋር መግባባት ተፈጥሯል ተብሏል።

በዚኹ ወር የውክልና ሥራቸውን የከወኑት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ሙባረክ ኤልያስ ሲሆኑ፣ እርሳቸውም ወደ **ቤኒ ሻንጉል ጉምዝ** ክልል ተጉዘው ከመራጮቻቸው ጋር ተወያይተዋል ተብሏል። አሥፈፃሚ አካሉ የሕዝቡን የልማት ጥያቄ ለመፍታት እያደረገ ያለው ጥረት የሚበረታታ መሆኑን ያነሱት እንደራሴው፣ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የተጀመሩ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል ይገባል ብለዋልም ተብሏል።



የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልና የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ም/ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ ሙባረክ ኤልያስ እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት አፈጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ አስካለች አልቦሮ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከመራጩ ሕዝብ ጋር ሲወያዩ




የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ፣ የተከበሩ ዶ.ር. ምህረቱ ሻንቆ እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ አገኘሁ ተሻገር ከአምባሳደር ጸጋዓብ ከበበው ጋር በ151ኛው ዓለም አቀፍ ፓርላማዊ ህብረት መደበኛ ጉባኤ

# የፓርላማ ዲፕሎማሲ

የ ኢትዮጵያ እንደራሴዎች በዚኹ ወርኃ ጥቅምት፣ አራት ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲዎችን አከናውነዋል። በዕለተ ጥቅምት ዐሥራ አንድ ወደ ሲወዘርላንዷ ጄኔቫ ከተማ የተጓዙት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ተጠሪው የተከበሩ ዶ.ር. ተሰፋዬ በልጅጌ፣ ምክትላቸው ዶ.ር. ምህረቱ ሻንቆ እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ አገኘሁ ተሻገር፣ በእነዚያ ቀናት በከተማዋ በተካሄደው **ዓለም ዓቀፍ ፓርላማዊ ኅብረት** ጉባኤ ላይ መሳተፋቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ያመለክታል። በጉባኤው ላይ፣ በርካታ ዓለም ዓቀፋዊ ፈተናዎች በበዙበት በዚኽ ዘመን ኢትዮጵያ ኹለንተናዊ ዕድገት እያስመዘገበች እንደምትገኝ የገለጹት ዶ.ር. ተስፋዬ፣ በጉባኤው ላይ የኢትዮጵያን አቋሞች፣ መሠረታዊ ዕሳቤዎች እና አገራዊ የለውጥ አጀንዳዎችን ለዓለም ማኅበረሰብ አንፀባርቀናል ብለዋል ተብሏል። ከ180 በላይ የተለያዩ የዓለም አገራት የእንደራሴ ምክር ቤቶች አባል እንደሆኑበት የተጠቀሰው ድርጅቱ፣ በምክር ቤቶች መካከል የውይይት እና የትብብር ግንኙነትን ማበረታታት፣ የዴሞክራሲ እና ሰብዓዊ መብት ጉዳዮችን እና ሌሎችም ተያያዥ ሐሳቦችን አጀንዳው አድርጎ እንደሚሰራም ተጠሪው ማብራራታቸው ተዘግቧል።

ኹለተኛው የእንደራሴዎቹ የወሩ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ክንውን፣ የኹለትዮሽ ትብብርን እና ቀጣይ አጋርነትን ለማጠናከር ያለመ የተባለው እና **በኢትዮጵያ እና በአርጀንቲና** መካከል የተካሄደው ውይይት ነበር። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የአርጀንቲናውን አምባሳደር ተቀብሎ ባወያየበት በዚኹ ወቅት፣ የኹለቱ አገራት የረጅም ጊዜ ዲፕሎማሲያዊ እና ኢኮኖሚያዊ ትስስር እንዲኹም፣ በንግድ፣ ቴክኖሎጂ፣ አቪዬሽን፣ ቱሪዝም እና በግብርና ዘርፎች ያላቸውን ሰፊ ትብብሮችን የበለጠ ለማጠናከር የሚያስችሉ የተሰኙ ጉዳዮች ተነስተው ሰፊ ውይይት ተደርጎባቸዋል ተብሏል፡፡ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የደቡብ አሜሪካ እና የካሪቢያን ፓርላማ ወዳጅነት ቡድን ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. አብዱልቃድር ገልገሎ፣ ኢትዮጵያ እና አርጀንቲና ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረ ታሪካዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዳላቸው አንስተው፣ ኢትዮጵያ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆን በምታደርገው ጥረት የአርጀንቲና ድጋፍ እንዳልተለያት መናገራቸውን ዘገባው ጠቅሷቸዋል። የአርጀንቲናው አምባሳደር ጁዋን ኢግናሲዮ ሮካታግሊታ በበኩላቸው፣ አርጀንቲና ከኢትዮጵያ ጋር በትምህርት፣ ስፖርት፣ ንግድ እና በግብርና ዘርፎች በጋራ እየሰራች መሆኑን አንስተው፣ በቀጣይም ይኽንኑ በይበልጥ አጠናክራ እንደምትቀጥል አረጋግጠዋል ተብሏል።

ሦሥተኛው የእንደራሴዎቹ ፓርላመንተሪ ዲፕሎማሲ፣ አዲስ አበባ ውስጥ ጥቅምት 19 2018 ዓ.ም. የተካሄደውን **የምሥራቅ አፍሪካ የፓርላማዎች ኅብረት ጉባኤ** የተመለከተው የእንደራሴዎቹ ተሳትፎ ነበር። በጉባኤው መክፈቻ ላይም፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ሰለሞን ላሌ፣ በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በተከናወኑ ተግባራት ለውጥ ማምጣት መቻሉን ተናግረዋል ተብሏል። የኅብረቱ የምግብ ዋስትና እና ሥነ-ምግብ ደኅንነት የኢትዮጵያ ተጠሪው የተከበሩ ዶ.ር. ንጉሤ መሸሻ በተራቸው፣ በኢትዮጵያ በምግብ እና ሥነ-ምግብ ደኅንነት ዙሪያ በተመዘገቡ ብሔራዊ ስኬቶች እና ሥራዎች ዙሪያ ለአባል አገሪቱ የአገራቸውን ልምድ ማካፈላቸውን ዘገባው ያመለክታል።



በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የደቡብ አሜሪካና የካሪቢያን ፓርላማ ወዳጅነት ቡድን ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አብዱልቃድር ገልገሎ እና በኢትዮጵያ የአርጀነቲና አምባሳደር አቶ ጁዋን ኢግናሲዮ ሮካታግሊታ

የወርኃ ጥቅምቱ የመጨረሻው የእንደራሴዎቹ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ **በኢትዮጵያ እና በፖላንድ** ዘላቂ ግንኙነት ዙሪያ እንደነበር ተጠቅሷል። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው፣ የፖላንድ የፓርላማ ልዑክን ተቀብሎ ባነጋገረበት ወቅት፣ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ አገራቱ ረጅም ዓመታትን ያሰቆጠረ ታሪካዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዳላቸው አንስተው፣ ኢትዮጵያ እነዚኽን ግንኙነቶች አጠናክራ የማስቀጠል ፍላጎት እንዳላትም ጠቁመዋል ተብሏል። የኮሚቴው አባል የተከበሩ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ በበኩላቸው አገሪቷ በትምህርት እና ሳይንስ ዘርፎች ሰፊ ልምድ እንዳላት አንስተው፣ በእነዚኽ እና በሌሎች መስኮች የበኩሏን ድጋፍ እንድታደርግ ጥሪ አቅርበዋል። በኢትዮጵያ የፖላንድ አምባሳደር ኢሎና ኮርቹት በበኩላቸው፣ አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር የነበራትን ዘርፈ ብዙ የዲፕሎማሲ እና የወዳጅነት ግንኙነት በይበልጥ አጠናክራ እንደምትቀጥል ማረጋገጣቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ጠቁሟል።



የሰላም እና የውጪ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴው፣ የፖላንድ ልዑክን ባነጋገረበት ወቅት፤



# እንደራሴዎቹ ስለ‘ራሳቸው በ‘ራሳቸው

የኢፌዲሪ እንደራሴዎች፣ የአዲሱን ዓመት ኹለተኛ ወር ያጠናቀቁት፣ ከላይ የተጠቀሱትን ሕገ-መንግሥታዊ ተግባራቸውን በመፈፀም ብቻም ሳይሆን፣ ምክር ቤታቸውን እና ራሳቸውን የሚመለከቱ ጉዳዮችንም በማከናወን ነበር።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤቱ የአስተባባሪ ኮሚቴ፣ የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድን መነሻ በማድረግ የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የአሥተዳደር ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሐፊ እና የዋና ጸሐፊው ተወካይ አቶ ከረዩ ባናታ፣ ዕቅዱን ለአስተባባሪ ኮሚቴው አቅርበው የኮሚቴው አባላትም ሰፊ ውይይት ማድረጋቸው ተዘግቧል። በዚያ የውይይት መድረክ ማጠቃለያ ላይ የተገኙት አፈ-ጉባኤው ታገሰ ጫፎ፣ ኢትዮጵያዊያን የአገር አንድነትን ለማጽናት ተባብረው እየሠሩ መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል። አፈ-ጉባኤው አክለውም፣ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ የጀመረውን ሥራ በተያዘለት ጊዜ እንዲያጠናቀቅ እና 7ኛው አገራዊ ምርጫ በመጪው ግንቦት ወር እንዲከናወን ምክር ቤቱ የበኩሉን ድጋፍ እያደረገ በመሆኑ፣ በ2018 በጀት ዓመትም አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን አስረድተዋል። ከዚኽ ባለፈም፣ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ ኢትዮጵያ ያነሳችው የባሕር በር ጥያቄ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ እንጂ በኃይል ባለመሆኑ፣ የተለያዩ አገራትም ትክክለኛ ጥያቄ መሆኑን እየደገፉት ስለሆነ የምክር ቤት አባላት በሚያደርጉት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ማስገንዘባቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል። ምክትል አፈ-ጉባኤዋ የተከበሩ ወይዘሮ ሎሚ በዶም፣ በምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት በተሠራው ማሻሻያ የሥራ አካባቢው ምቹ እንዲሆን የተጀመረውን ሥራ አጠናክሮ በማስቀጠል፣ የምክር ቤት አባላት ሕግ ሲያወጡም ሆነ ክትትል እና ቁጥጥር ሲያደርጉ ጽሕፈት ቤቱ የሚያደርገው አሥተዳደራዊ እና ሙያዊ ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አስገንዝበዋል ተብሏል። ሌላይኛው እንደራሴ እና የመንግስት ተጠሪው የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ፣ የኑሮ ውድነትን እና የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስ፣ የሥራ ፈጠራን እና የፕሮጀክቶችን አፈጻጸሞች ለማሻሻል መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ በመሆኑ፣ እንደራሴዎቹም የሚያደርጉትን የክትትል እና የቁጥጥር እንዲኹም ድጋፍ አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ማሳሰባቸው ተዘግቧል።

በዚኹ ጥቅምት ወር፣ እንደራሴዎቹ ስለ ‘ራሳቸው ከከወኗቸው ተግባራት አንዱ የክረምቱን የውክልና ሥራ መገምገም ነበር። በዚኽም ግምገማ ላይ የተገኙት አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ በሕዝብ ውክልና ሥራው የተነሱ ጥያቄዎችን ለሚመለከታቸው ተቋማት አከፋፍሎ በመስጠት እና አፈጻጸማቸውን በመከታተል ለጥያቄዎቹ ምላሽ የሰጡ ተቋማት የሚመሰገኑበት እና በቂ ምላሽ ያልሰጡት ደግሞ የሚጠየቁበት ሥርዓት ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ መናገራቸው ተሰምቷል። የእንደራሴዎቹን ምክር ቤት አሠራር ለማዘመን ከሌሎች አገራት መልካም ተሞክሮዎችን ለመቀመር የጥናት ኮሚቴ ተቋቁሞ እየሠራ መሆኑን መጥቀሳቸው የተዘገበው ደግሞ ምክትል አፈ-ጉባኤዋ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ ነበሩ። የውክልና ሥራውን ሪፖርት ያቀረቡት ረዳት የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትሯ ወ/ሮ መሠረት ኃይሌ ሲሆኑ፤ እርሳቸውም፣ መንግስት ከመስኖ ልማት እና ከሌማት ትሩፋት እንቅስቃሴዎች አንፃር በርካታ ውጤታማ ሥራዎች እንደተሰሩ ጠቅሰው፣ የፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎችም አመራሩ ከመቼውም በላይ በተሻለ ቁርጠኝነት ፀጥታውን ወደነበረበት ለመመለስ እየሠራ እንደሆነ ጠቁመዋል ተብሏል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ወጪ፣ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በ2018 ዓ.ም. የኦዲት ባለድርሻ አካላት የትብብር ፎረም ረቂቅ ዕቅድ ላይ ያደረገው ውይይት፣ አንዱ የእንደራሴዎቹ የ‘ራስ በራስ መድረክ ነበር። የፎረሙን ረቂቅ ዕቅድ ያቀረቡት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. የሺመቤት ደምሴ ሲሆኑ፤ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶች እና መፍትሔዎች እንዲኹም የክትትል እና የቁጥጥር ሥራዎችን በዝርዝር ገልፀዋል ተብሏል። በውይይቱ ላይም ከተለያዩ ተቋማት የመጡ ባለድርሻ አካላት ለቋሚ ኮሚቴው በዕቅዱ ላይ አስተያየት እና ጥያቄዎችን ሰንዝረው ውይይት እንደተደረገባቸው ተዘግቧል።

እንደራሴዎቹ፣ ወሩን ሊያጠናቅቁ ሲዳረሱ፣ በምክር ቤቱ ውስጥ ለሚገኙ የተወሰኑ ቋሚ ኮሚቴ አመራሮች እና የፐብሊክ በጀት ጥናት፣ ትንተና ምርመራ መሪ ሥራ አሥፈጻሚ ዴስኮች ሥልጠና መሰጠቱንም ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። አዳማ ለከተሙት ለኘላን፣ በጀት እና ፋይናንስ እና ለመንግሥት ወጪ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴዎች፣ እንዲኹም ለምክር ቤቱ ኃላፊዎች የተሰጠው ሥልጠና፣ የመንግሥት በጀት ዕቅድ ዝግጅት፣ በጀት አፀዳደቅ እና የአሥፈጻሚ ተቋማት በጀት አጠቃቀምን የተመለከተ እንደነበረም መረጃው ይጠቁማል። በሥልጠናው ላይም፣ የበጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ እና ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም አለማየሁ እንዲኹም የንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች ተሳትፈዋል ተብሏል።

## የእንደራሴዎቹ ጉብኝት

የኢፌዴሪ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ከፍተኛ አመራሮች፣ የምክር ቤቱ አማካሪ ኮሚቴ አባላት፣ የቋሚ ኮሚቴዎ አመራሮች እና አባላት እንዲኹም የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊዎች፣ ታላቁን የሕዳሴ ግድብ የጎበኙበት ኹነትም አንዱ የወሩ የሚጠቀስ ክንውናቸው ነበር። የሕዳሴ ግድብ ዜጎች ዋጋ የከፈሉበት ታላቅ ፕሮጀክት ነው ሲሉ የተደመጡት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ፣ የሕዳሴ ግድብ የዜጎች የላብ ጠብታ፣ የደም ጠብታ እና የውኃ ጠብታ ውጤት ነው ብለዋል ተብሏል። አፈ-ጉባኤዋ አክለውም፣ ኢትዮጵያ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲዋ ብቻዋን የመልማት ፍላጎት የሌላት እና ቅድሚያ ለጎረቤት አገራት የምትሰጥ መሆኗን ተናግረዋል፡፡ ከጉብኝታቸው መለስ ስለ ባሕር በር ጥያቄም ያነሱት የተከበሩ ሎሚ፣ የባሕር በር ዝም ብሎ እንደ ተራ ሸቀጥ የሚታይ አይደለም ሲሉም ተሰምተዋል። ወ/ሮ ሎሚ ለጥቀውም፣ ምክር ቤቱ በጉዳዩ ላይ በቂ ግንዛቤ በመያዝ ሕጎችን በመደሰስ እና በማውጣት፣ የፓርላማ ዲፕሎማሲን በማጠናከር አገሪቱ የባሕር በር ባለቤት እንድትሆን የተጠናከረ ሥራ እንደሚሰራም ማብራራታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትሯ የተከበሩ ወ/ሮ መሰረት ኃይሌ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ የተፋሰሱ አገራት ከሕዳሴ ግድብ ፍትሐዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የነበራትን አቋም በተግባር ያሳየች እና አኹንም ያልተቀየረ አቋሟን የውኃውን ፍሰት ባለመቀነስ በተጨባጭ ማስመስከሯን ገልፀዋል ተብሏል።



የምክር ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች፣ የምክር ቤቱ አማካሪ ኮሚቴ አባላት፣ የቋሚ ኮሚቴዎች አመራሮች እና የጽህፈት ቤቱ ኃላፊዎች ታላቁ የህዳሴ ግድብ ጉብኝት



የሠንደቅ ዓላማ ቀን ሲከበር፤

# ታላቁ ቀን

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በዚኹ ዓመት ጥቅምት ወር ላይ የተከበረውን የሠንደቅ ዓላማ ቀን ደመቅ ባለ ኹኔታ አክብረዋል። የፌዴሬሽኑ ፕሬዝደንት የተከበሩ ታዬ ታዬ አፅቀሥላሴ በተገኙበት ጥቅምት ሦሥት ቀን፣ "ሠንደቅ ዓላማችን ለኢትዮጵያ ታላቅ የከፍታ ዘመን ብሥራት፣ ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለሉዐላዊነታችን እና ለኢትዮጵያ ሕዳሴ!" በሚል መሪ ቃል ማክበራቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ይጠቁማል። ፕሬዝደንቱም፣ ዘመኑ የኢትዮጵያ ታላቅ የብሥራት እና የከፍታ ዘመን ነው ሲሉ ተደምጠዋል። ለ18ኛ ጊዜ በተከበረው በዚኽ በዓል፣ ሠንደቅ ዓላማ ትውልዱ የአገር ፍቅር እና ቃል ኪዳን የሚያድስበት፣ የጋራ ዕድገት የሚጎለበት፣ የነገ ተስፋ የሚፀናበት ታላቅ ብሔራዊ በዓል ነው ያሉት ፕሬዝደንት ታዬ፣ የህልውና ፈተናዎችን በሕዝቦች አንድነት በማለፍ፣ ኢትዮጵያ የመወሰን ብቃቷን እያስመሰከረች ትገኛለችም ብለዋል ተብሏል።

በዚኹ የሠንደቅ ዓላማ ክብረ-በዓል ላይ የተገኙት የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ ሠንደቅ ዓላማችን ቃል ኪዳናችንን የምናፀናበት፣ ብሔራዊ የአርበኝነት መንፈሳችንን የምንቀሰቅስበት እና የምናድስበት ታላቅ አገራዊ በዓል መሆኑን ሲሉ መናገራቸውን ዘገባው ጠቅሷቸዋል። የውስጥ እና የውጭ ጠላቶች ሊሰብሩት የማይችሉት የኅብረ ብሔራዊ አንድነት እና ሉአላዊነት ማሳያ ነው ሲሉ ያከሉት አፈ-ጉባኤው፣ የሠንደቅ ዓላማ በዓል ሲከበር በታሪክ ውጣ ውረድ ውስጥ የጽናታችን ምልክት እና ለአገር ብልጽግና እና ዘለቄ ልማት ያለንን ጽኑ አቋም ወደ ብሩህ ከፍታ ዘመን ያሻገርን መሆኑን የምናውጅበት ነው ብለዋልም ተብሏል።



ፕሬዝደንቱ እና እንደራሴዎቹ በክብረ-በዓሉ ወቅት፤

# የብሪጅ አጭር ዳሰሳዊ ምልከታ በእንደራሴዎቹ ውክልና ዙሪያ

## እንደራሴነት

ዘመናዊ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ከተጀመረ አንስቶ፣ የእንደራሴዎች ምክር ቤቶች የውክልና ዲሞክራሲ ተቋማዊ መገለጫ ሆነው አገልግለዋል። ዋና ተግባራቸው የሆነው ተወካይነት በታሪክ፣ ፖለቲካዊ እና በማኅበራዊ ለውጦች እየተቀረጸ በጊዜ ሂደት ከፍተኛ ለውጥ ማሳየቱን በርዕሰ-ጉዳዩ ላይ የተጸፉ ድርሳናት ይጠቅሳሉ። ከጥንታዊ የአማካሪ ምክር ቤቶች አንስቶ እስከ ዘመናዊ የሕግ አውጪ አካላት ድረስ፣ ምክር ቤቶች ዜጎችን ከመንግሥት ጋር በማገናኘት ያላቸው የአገናኝነት የውክልና ሚና እየተሰፋፋ ሄዷል። ድርሳናቱ እንደሚጠቅሱት፣ አስቀድሞ የተወካይነት ጽንሰ-ሐሳብ የተመሠረተው የተመረጡ ባለሥልጣናት የዜጎችን ፍላጎት ወክለው የሚሠሩበት እና ቀጥተኛ የመራጭ-ተመራጭ መስተጋብር ውስን በሆነበት አውድ ላይ ነበር። በቅርብ ዐሥርታት ውስጥ ይህ የግንኙነት መስተጋብር ይበልጥ ተለዋዋጭ እና አሳታፊ ወደመሆን ተሻግሯል። በሂደትም፣ መራጮች እንደራሴዎቻቸውን ተደራሽ፣ ምላሽ ሰጪ እና ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚጠብቁባቸው በወቅት ተኮሩ ምርጫ ወቅት ብቻ ሳይሆን፣ በዘመነ-እንደራሴነታቸው ጭምር ሆኗል።

በዚኽ ሂደት ያለፈው የእንደራሴዎች ምክር ቤቶች ተቋማዊ ቅርጽ፣ የትኛውም አገር ከሚከተለው የዲሞክራሲ ፍልስፍና ጽንሰ ሐሳባዊ ልዩነቶች እና ታሪካዊ የተቋማዊነት መለዮዎች ልዩነቶች ባለፈ፣ መሠረታዊ የሚባሉ ተመሳስሎሾች አሏቸው። በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉትም፣ ለዚያች አገር ይበጃሉ የተባሉ ሕግጋትን ማውጣት፣ መንግሥት የተሰኘው ሥራ አሥፈጻሚ አካል፣ የወጡትን ሕግጋትን እና ፖሊሲዎችን በሚገባ እየተገበረ መሆኑን መከታተል እና መቆጣጠር፣ የራሱን ምክር ቤት እንደራሴዎች የተወካይነት ሚናን በሕግጋት ከማጽደቅ ባሻገር ከመራጮቻቸው ጋር ቀጥተኛ የግንኙነት ሂደቶችን መፍጠር እና ያንን የግንኙነት መስተጋብር ሥራ አሥፈጻሚውን ለመግራት ጭምር መተርጎሚያ ማድረግ የሚሉት ቀዳሚዎቹ የእንደራሴ ምክር ቤቶች የመመሥረት ፋይዳ ተደርገው ተወስደዋል።

የምክር ቤቱ ገጽታ በዚኽ መልኩ ተቋማዊ ልውጠቱን ቢያገኝም፣ የሚከውናቸው የውክልና ተግባራት የሚወሰኑበት፣ ከአገር አገር የተወሰኑ ሂደታዊ ልዩነቶች አሉት። እነዚኽ በጥናታዊ ሥራዎች የውክልና ትግበራ ቅርጾች ተብለው ሲጠሩ፣ ቀዳሚውን ቅርጽ ቀጥተኛ ተሳትፎ ብለው ይጠሩታል። ለዚኽ በማሳያነት የብሪታኒያን ምክር ቤት በማሳያነት የሚያነሱት ጸሓፍት፣ በእነዚኽ መሰል አገራት ያሉ እንደራሴዎች፣ የውክልና ግብራቸውን ለመፈጸም በ'የምርጫ አካባቢዎቻቸው ጽሕፈት ቤቶችን የማቋቋም ግዴታ እንዳለባቸው ይጠቀሳሉ። እንዲኹም የዜጎችን ቅሬታ ለመስማት መደበኛ የሕዝብ ሐሳቦችን መቀበያ ክፍለ-ጊዜያትም ያበጃሉ። በኹለተኛ ማሳያነት የሚነሳው ደግሞ፣ የተመጣጣኝ የምርጫ ሥርዓትን በሚተገብሩ ሥርዓቶች ውስጥ የሚስተዋለው ዓይነት ሲሆን፤ ይኽም በዋናነት በፓርቲ መዋቅር ላይ እንደሚመሠረት አጥኚዎቹ ያነሳሉ። ይኽን መሰሉ የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት ባላቸው አገሮች ውስጥ፣ መራጭ ዜጎችን የማሳተፍ ሚና በአብዛኛው ከእንደራሴዎች የግል ተሳትፎ ይልቅ፣ በፓርቲ መዋቅሮች ላይ ይወድቃል። ያም ሆኖ፣ ተቋማዊ ቅርጹ እነዚህ መሰል ልዩነቶችን ቢያንጸባርቅም፣ በእንደራሴዎች እና በሕዝብ መካከል ወደ ይበልጥ ቀጥተኛ እና ትርጉም ያለው መስተጋብር የመሸጋገር አዝማሚያው ዓለም ዓቀፋዊ መልክ እንዳለው ይታመናል።

# ወደ ኢትዮጵያ

ሦሥት መንግሥታትን ያየው የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት ግንባታ ሂደት፣ አሁን ያለውን መልክ ለመያዝ ብዙ ሂደቶችን መሻገሩ ግልጽ ነው። የአጼውን ሥርዓት ዘመናዊ ገጽታ ለማልበስ ተጀምሮ፣ የደርግን ጥብቅ ከላይ ወደታች የሚዘረጋ ሶሻሊስታዊ ሥርዓተ-መንግሥትን ለማንበር አንድ ዐሥርትን ፈጅቷል። አኹን ያለው ምክር ቤት፣ የ1987ቱን የፌደራሊዝም ጅማሮ ተከትሎ፣ በተለያዩ የለውጥ ማዕቀፎች ውስጥ በማለፍ፣ የዛሬውን ገጽታ ይዟል።

አኹን ያለው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ምንም እንኳን ገዢው ብልጽግና ፓርቲ አብላጫ ወንበር ቢይዝበትም ጥቂት የተፎካካሪ ፓርቲ አባላትንም አቅፏል። በሥድስተኛው አገራዊ ምርጫ የተቋቋመው ይኽ ምክር ቤት፣ ካሉት 547 መቀመጫዎች፣ በምርጫው የተያዙት 481 የሚሆኑት ናቸው። ለዚኽ የቁጥር ልዩነቶች አስተዋጽዖ ያደረጉት በትግራይ ክልል ሙሉ ለሙሉ ምርጫ አለመደረጉ እና በአማራ፣ ቤኒ ሻንጉል ጉምዝ፣ አፋር እና ሌሎች የምርጫ አካባቢዎች ምርጫ አለመደረጉ መሆኑ ይታወቃል። ይኽም ሆኖ፣ ከኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ እስከ የጌዲዮ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት፤ ከየቁጫ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ እስከ የጉምዝ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ እና የቦሮ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ የደረሱ የተፎካካሪ ፓርቲ ተመራጮችን ማካተቱን የምክር ቤቱ መረጃ ያሳያል። 279 ወንዶችን እና 201 ሴት እንደራሴዎችን የያዘው ምክር ቤቱ፣ ለእያንዳንዱ እንደራሴ ቢያንስ የኹለት መቶ ሺ ዜጎችን የመወከል ሕገ-መንግሥታዊ ኀላፊነት ሰጥቷል። ያም ማለት፣ እያንዳንዱ እንደራሴ፣ በዚኽ መጠን የሚደርሱ ዜጎችን ጥያቄዎች፣ ቅሬታዎች እና የመልካም አሥተዳደር መሻቶችን ማድመጥ ብቻም ሳይሆን የቅሬታዎቹን አፈታት እና አተገባበር የመከታተል ከበድ ያለ ኀላፊነት ተጥሎበታል።

## የውክልናው ገጽታዎች

የወርኃ ጥቅምት እንደራሴ ዕትማችን ርዕሰ-ጉዳይ ያደረግነውን የሕዝብ ውክልና በዚኽ አውድ ለመመልከት ስንሞክር፣ የሚነሱ ጥቂት ተቋማዊ ገጽታዎችን እናገኛለን። በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ ዐራት፣ ተገዢነታቸው ለሕገ-መንግሥቱ፣ ለሕዝቡ እና ለህሊናቸው መሆኑ የሚጠበቅባቸው እንደራሴዎቹ፣ እነዚኽን ሦሥት ክቡድ ኀላፊነቶች የሚወጡበት ዓይነተኛው መንገድ የሕዝብ ውክልና መሆኑ ግልጽ ነው። ይኽን ኀላፊነታቸውን የሚተገብሩበትን ተቋማዊ አሠራርንም መመልከት ሙሉ ስዕል ለማግኘት ጠቃሚ ይመስለናል።

እንደ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት ደንብ ከሆነ፣ እንደራሴዎቹ ለውክልና ሥራቸው ከመራጮቻቸው ጋር ከተገናኙ በኋላ፣ መራጮቻቸው ያነሷቸውን የትኞቹንም ሕጋዊ ጉዳዮች ለምክር ቤቱ የሚያቀርቡበት ሥርዓታዊ ደንብ ተዘርግቷል። እንደራሴዎቹ በዓመት ኹለት ጊዜ ለሚያደርጉት ይኽ የውክልና ሥራ፣ አስቀድመው ወደሚሄዱባቸው ምርጫ አካባቢዎች የሚገኙ የክልል አልያም የዞን የግንኙነት አካላትን ለመራጭ-ተመራጭ መድረኮቻቸው ስልጡነት እንዲያውቁም ይጠበቃል። እያንዳንዱ እንደራሴ፣ ከመራጮቹ ጋር በአካል ከተገናኘ በኋላ ለሚመለከተው የምክር ቤቱ አካል በዝርዝር የተቀመጡ መረጃዎችን የያዘ ሪፖርት የማዘጋጀት ግዴታ አለበት። ይኽ ሪፖርት፣ የሕዝብ ውክልናን ተጠያቂነትን እና ግልጽነትን ለማረጋገጥ እጅጉን አስፈላጊ ነው። እንደ ምክር ቤቱ የአሠራር ደንብ ከሆነም፣ ሪፖርቱን የሚያዘጋጀው እንደራሴ፣ የመራጭ-ተመራጭ መድረኮቹን ዝርዝር መረጃዎች፣ ማለትም የምርጫ ጣቢያውን ስም፣ በውክልና መድረኩ የተገኙ መራጮችን ብዛት፣ እንዲኹም በዋናነት ተወያዮቹ ዜጎች ያነሷቸውን ጥያቄዎች እና አስተያየቶች በዝርዝር ማካተት ይጠበቅበታል። ከዚህም በተጨማሪ፣ የተካሄደውን የውክልና ሥራ አስመልክቶ እንደራሴው የራሱን አጠቃላይ ምልከታዎች፣ ሕዝቡን ለማወያየት የተጠቀመውን የማወያያ ሥነ-ዘዴ፣ ከውይይቶቹ የተገኙትን ዋና ዋና ጭብጦች እና በውክልና ሥራው ወቅት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን እና መፍትሔዎችን ጨምሮ በግልጽ ማስፈር ይጠበቅበታል። ከዚኽ አለፍ ሲልም፣ ለሕዝብ ውክልና ሥራዎች ገንዘብ ወይም ቁሳቁስ የተመደበ ከሆነ፣ የሚመለከተው እንደራሴ የተመደበውን ሀብት አጠቃቀም ዝርዝርን በሪፖርቱ ውስጥ እንደሚያካትትም ይታሰባል። በዚኽ መልኩ የተዘጋጀው ከውክልና መለስ የተዘጋጀው ሪፖርት ለሚመለከተው የምክር ቤቱ ቡድን ከቀረበ በኋላ፣ ተቀባዩ አካል የተቀበላቸውን መረጃዎች በማጠቃለል፣ ለምክር ቤቱ ሊቀርቡ የሚገባቸውን ቁልፍ ጉዳዮች በመለየት፣ የጋራ ሪፖርትን ለአፈ-ጉባኤው ማቅረብ ይጠበቅበታል። ይኽን መሰሉ ሪፖርት በክልላዊ መንግስት ሥልጣን ሥር ያሉ ጉዳዮችን የሚያካትት ከሆነ፣ እንደራሴው ለሚመለከተው የአካባቢ ወይም የክልል አሥተዳደር የመረጃውን ጨመቅ የማጋራት ኀላፊነት አለበት ተብሏል። በዚኽ መልኩ ያገኟቸውን ቅሬታዎችም ሆነ የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች፣ የፌደራል መንግሥቱን ኀላፊነት የሚመለከቱትን በክልል አልያም በአካባቢያዊ አሥተዳደር ደረጃ ምላሽ ሊያገኙ የሚችሉትን ለይተው፣ ምላሽ መሰጠቱንም ለመከታተል የሚያስችላቸውን ሂደት የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ እና በምክር ቤቱ የሚገኙት ሦሥቱ የመንግሥት ተጠሪዎች እንዲያሳልጡላቸው ይጠበቅባቸዋል።

በዚኽ አጠር አድርገን ባነሳነው መልኩ ስለተካሄደው የውክልና ሥራ እንደራሴ ከምክር ቤቱ ያገኘው ቀጥራዊ መረጃ እንደሚጠቁመው፣ በ2017 ዓ.ም. የካተት ወር ብቻ በእንደራሴዎች የተካሄደው የውክልና ሥራ 62 በመቶ እንደተሳካ ይጠቅሳል። በደነቡ መሠረት በነሐሴ፣ በጷግሜ እና በነሐሴ ወራት የተካሄደው የውክልና ሥራ የእንደራሴ ዳሰሳ እንደሚያሳየው፣ የውክልና ሥራው ወደ 85 በመቶ የሚጠጋ ተፈጻሚነት አለው። እነዚኽ፣ በአገሪቷ የሚገኙ የትኞቹም ተቋማት መንግስታዊ ኀላፊነታቸውን በፍትሓዊነት ይጠቀሙ ዘንድ፣ በዋናነትም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በሕገ-መንግሥቱ የተሰጡ መብቶች ሳይሸራረፉ መተግበራቸውን ለመከታተል ኹነኛ ፋይዳ ያለው የውክልና ግብር፣ ተጠቃሽ ውጤቶችም፣ ሊሻሻሉ የሚችሉ ክፍተቶችም ተስተውለውበታል።

## ምን አሳኩ?

እንደራሴ፣ ይኽንን ጉዳይ አስመልክቶ ከሕዝብ ተወካዮቹ ምክር ቤት መዛግብት እና ከሌሎች ቀጥተኛ እና ኹለተኛ ምንጮች ያሰባሰበቻቸው መረጃዎች፣ በውክልና ሥራው የተለያዩ በስኬት የሚጠቀሱ ውጤቶች መታየታቸውን ተገንዝባለች። ዋና ዋና የምንላቸውን በማሳየነት እንጥቀስ፤

- የ2013ቱ ምርጫ ካልተካሄደባት ትግራይ ክልል ውጪ፣ በኹሉም ሊባል በሚችል ደረጃ ባሉት ክልሎች እና ኹለቱ የከተማ አሥተዳደሮች ያሉ ዜጎችን ድምጾች እንደራሴዎቹ መስማት መቻላቸው ተጠቃሽ ስኬት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል ብለን እናስባለን።
- መራጮች በውክልና ውይይቶቹ ወቅት ያሳስቡናል ያሏቸው ጥያቄዎች፣ ለፌደራል መንግሥቱም ሆነ ለሚመለከታቸው የፌደራል እና ክልላዊ ተቋማት ተደራሽ የሚደረጉበት ሂደት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መሄዱን እና ቁጥራቸው በዛ ያሉት ቅሬታዎችም ምላሽ እንዲያገኙ የተደረገበትንም ሁኔታ ማስተዋል ተችሏል።
- እንደ እንደራሴ ዳሰሳ፣ ብዙዎቹ የመራጭ-ተመራጭ መድረኮች፣ ከ'የአካባቢዎቹ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ ባለሥልጣናት እና የምክር ቤቶቹ አባላት ጋር በጋራ መደረጋቸው በጥንካሬ ሊጠቀስ የሚገባው ነው፤ ምክንያቱም፣ ይኽን መሰሎቹ መድረኮች፣ አንድ የፖለቲካ-ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ከመፍጠር አኳያ፣ በፌደራል መንግሥቱ እና በክልሎቹ መንግስታት መካከል ጠንካራ የጋራ ርዕይን ለመፍጠር ብቻም ሳይሆን፣ የፌዴሬሽኑ ዲሞክራሲያው ተቋማት ጥንካሬ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ እንዲሄድ እጅጉን ድርሻው ከፍ ያለ መሆኑ አሌ አይባልምና።
- አገሪቷ ከጀመረቻቸው ሰፊ አገራዊ ፕሮጀክቶች አኳያ፣ በ'የአካባቢው የሚገኘው ዜጋ፣ በቅርበት ይመለከተኛል የሚላቸውን ጉዳዮች በተለያዩ የውክልናው መድረኮች ላይ ማንሳቱን ያሰባሰብናቸው መረጃዎቹ ያሳያሉ። ይኽም፣ ጥያቄዎቹ ወደ ፌደራል መንግሥቱ እና የሚመለከታቸው ተቋማት እንደመድረሳቸው፣ ግዙፎቹን ፕሮጀክት ሕዝባዊ የባለቤትነት መንፈስን ለማስረጽ እና የአፈጻጸም ልኬታቸውን ለመቆጣጠርም አመቺ ሁኔታን ከመፍጠሩ አኳያ በእርግጥም፣ በጠንካራ ጎን ሊነሳ የሚችል የእንደራሴዎቹ የውክልና ግብር ነው።
- በብዙዎቹ የውክልና መድረኮች በተለይም፣ በወርኃ ነሐሴ በነበሩት ሰፋፊ የመራጭ ተመራጭ መድረኮች ሲነሱ የተስተዋሉት የሕዝቡ አስተያየቶች እና ጥያቄዎች፣ አሥፈጻሚ አካላትን ለመቆጣጠር ለእንደራሴዎቹ ምቹ የምዘና መስፈርቶችን የሚሰጡ መሆናቸውን ብሪጅ ተገንዝባለች። ከዚኽ አንጻርም፣ የእንደራሴዎቹ የውክልና ተግባራት ዳሰሳ የሚጠቀስ አዎንታዊ ውጤቱ ነው ተብሎ ሊነሳ የሚገባው ነው።
- በመቶዎች በሚቆጠሩት የሕዝብ ውክልና ሥራዎች ወቅት፣ አንዳንድ የመራጮች ጥያቄዎች የመንግሥትን አኹናዊ ቅድምና የሚወስዱ ፖሊሲዎችን እና የልማት አቅጣጫዎችን በቅጡ ካለመረዳት የመጡ እንደነበሩ የብሪጅ አጭር ዳሰሳ ይጠቁማል። ከዚኽ አኳያም፣ እንደራሴዎቹ ይኽን መሰሎቹን ጉዳዮች በሚገባ ለማብራራት መድረኮቹን ሲጠቀሙ ተስተውሏል፤ ይኽም ሊበረታታ የሚገባው ተጠቃሽ የውክልና ሥራው ውጤት ነው።

# ክፍተቶች እና የብሪጅ ምክረ-ሐሳቦች

የቀደመው ዓመት የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የሕዝብ ውክልና ሥራዎች ከላይ አጠር አድርገን የጠቀስናቸው ተጠቃሽ ውጤቶች ቢኖሩትም ቅሉ፣ ተጨማሪ ሥራዎች የሚያሻቸው ክፍተቶችም ታይተውበታል፤ መፍትሔ ይፈልጋሉ የምንላቸውን እኒኽን ተግዳሮቶች፣ ከተቋማችን ተጨባጭ የመፍትሔ ሐሳቦች ጋር ብንመለከታቸው፣ ቀሪ የምክር ቤቱን ሥራ ያቀላል ብለን እናምናለን። ለመጥቀስ ያህልም፦

- የኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የ5ዓመት መሪ ዕቅድ ረቂቅ ሰነድ እንደሚጠቅሰው እንኳ፣ በተለያዩ ምክንያቶች የሕዝብ ውክልና ሥራቸውን የማይወጡ እንደራሴዎች ታይተዋል። ከላይ እንደጠቀስነው የሚወክሉት ሕዝብ ከ200 ሺሕ የማይንስ ከመሆኑ አኳያ፣ ይህን ያህል መራጭ ድምጹን የሚያሰማበት መድረክ መነፈጉ አንዱ የአተገባበር ክፍተት ሆኖ ሊቆጠር ይችላል። እናም፣ ይኽን መሰሉ ተግባር የታየባቸው እንደራሴዎችን ምክር ቤቱ በአሠራር ደንብ እና መመሪያ በመመርኮዝ እርምት እንዲያደርጉ ቢያደርግ የውክልና ሥራው ከዚኽ የተሻሉ ውጤቶች ይታዩበታል ብለን እናምናለን።
- በቀደመው ዓመት በተከናወኑት የሕዝብ ውክልና ሥራዎች እንዳስተዋለነው፣ ከመራጮቹ በኩል ሲነሱ የሰነበቱት ጥያቄዎች በዋናነት ከአካባቢ ተኮር የመልካም አሥተዳደር ጉድለቶች፣ በተለይም በዋጋ ንረት በሚገፋው የኑሮ ውድነት፣ የመሠረተ-ልማቶች በተቀመጠላቸው ቀነ-ገደብ አለመጠናቀቅ እና አነስተኛ ቢሆኑም ቅሉ እዚኽም እዚያም የሚስተዋሉ የሰላም መደነቃቀፎች መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል። እነዚኽን የሕዝቡን ጥያቄዎች ለመፍታት ደግሞ፣ እንደራሴዎቹ በወርኃ የካቲት የተነሱትን ጥያቄዎች በነሐሴ እና በመስከረም ወራት መፈታት አለመፈታታቸውን ለማረጋገጥ የሚመለከታቸው ተቋማት ላይ ብርቱ ቁጥጥር ማካሄድ ያስፈልጋቸዋል። እናም፣ እዚኽ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ እንደራሴዎቹ ያልተቋረጠ ክትትላቸውን ከዚኽ የበለጠ ቢያደርጉ ችግሮቹ የሚቀረፉበትን መንገድ ያቀላልና የሚመለከታቸው የምክር ቤቱ አካላትም ለመፍትሔው ድጋፋቸውን ይበልጥ እንዲያጠናክሩ ስትል ብሪጅ ጥሪ ማድረግ ትሻለች።
- የእንደራሴዎች የሕዝብ ውክልና ሥራ፣ የምክር ቤቱ ተጠያቂነት የማዕዘን ድንጋይ መሆኑ ይታወቃል። ከዚኽ አንጻርም፣ እንደራሴዎቹ ከወከላቸው ሕዝብ ጋር የሚገናኙባቸው መንገዶች በከፊልም ቢሆን ክፍተቶች የሚታዩበት ይመስላል። ይኽም ማለት፣ ከስልክ እስከ ፋክስ እና የማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮች ድረስ ያሉ የመገናኛ አማራጮችን ተወካዮቹ ሙሉ ለሙሉ ለውክልና ሥራቸው ተጠቅመዋል ማለት የሚያስደፍር አይደለም። በእርግጥ ይኽ ዕግዳት፣ እንደሌሎቹ የአገሪቷ ተቋማት ኹሉ ምክር ቤቱን የተለየ ባያደርገውም፣ የእንደራሴዎቹን የውክልና ሥራ በጥቂቱም ቢሆን ሳያደናቅፈው አልቀረም። ስለዚኽም በብሪጅ ዕምነት፣ እኒኽን መሰል የመራጭ-ተመራጭ መገናኛ አማራጮችን፣ ምክር ቤቱ ከሚመለከታቸው የፌደራል እናአ የክልል ተቋማት ጋር በመሆን፣ ከዚኽ ይበልጥ የሚሻሻሉበት እና አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን የሚጠቀሙበትን አካሄድ ይብለጥ ቢገፋበት ፍይዳው ብዙ ነው የሚለው የብሪጅ አንዱ ምክረ-ሐሳብ ነው።
- የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በያዝነው ዓመት በስኬት ሊቆጠርለት የሚገባው አንድ ተግባሩ የራሱን የቴሌቪዥን ጣቢያ ማቋቋሙ ነው። ከዚኽ ቀደም የነበሩት የሕዝብ ውክልና ሥራዎች አደባባይ ይውሉ የነበረው በዜና ሪፖርታዥ ደረጃ በምክር ቤቱ ማኅበራዊ ሚድያዎች ነበር። ነገር ግን አኹን ይኽ ጣቢያ መኖሩ፣ የሕዝብ ውክልና ሥራዎችን በዚኽ የሚዲያ አማራጭ ለማስተላለፍ መልካም አጋጣሚዎችን ፈጥሯል። ይኽ ሂደትም፣ ሕዝቡ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች ሥራ አሥፈጻሚውም ሆነ የሚመለከታቸው የክልሎቹ ተቋማት፣ ቅሬታዎቹን ሰምተው ለመፍትሔ የሚያደርጓቸውን ጥረቶች ሕዝቡ እንዲከታተላቸው ኹነኛ የክክትል አማራጭ ነውና፣ ቢታሰብበት ስትል ብሪጅ ጥያቄዋን ማስተላለፍ ትሻለች።
- እንደሚታወቀው፣ የትግራይ ክልል እና ሌሎች አነስተኛ አካባቢዎች ምርጫ ሊደረግ የሚችልበት አስቻይ ሁኔታ ባለመኖሩ የተነሳ ተወካዮቻቸውን ወደ ምክር ቤቱ አላኩም። ይኽ አስገዳጅ ኹኔታም፣ በእነዚኽ አካባቢዎች ያሉ ዜጎች ወደ ፌደራል መንግሥቱም ሆነ የአካባቢው አሥተዳደሮቻቸው እንዲመልሱላቸው የሚሿቸውን ጥያቄዎች ወደ ምክር ቤቱ መድረኮች ማምጣት እንዳይቻል አድርጎታል። ስለዚኽም፣ ምንም እንኳን ቀጣዩ ምርጫ በያዝነው ዓመት ይደረጋል ተብሎ ቢታመንም፣ እስከዚያው ጊዜ ድረስ ባሉት ወራቶች የእነዚኽ አካባቢ ድምጾች ለቀሩት እንደራሴዎች የሚሰሙበትን አንዳች የግኙነት መላ የሚመለከታቸው የምክር ቤቱ አካላት አበክረው ቢያስቡበት ጠቀሜታው ብዙ መሆኑን ማስታወስ እንሻለን።
- በኢትዮጵያ እንደራሴዎች የሕዝብ ውክልና ሥራዎች ላይ የተሰሩ የራሱ የምክር ቤቱ የውስጥ እና የውጪ ጥናቶች፣ ከመራጭ-ተመራጭ መድረኮች ተሳታፊነት አኳያ የሴቶች እና በተለይም የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ መሻሻል የሚያስፈልገው አነስተኛ ክፍተት እንደሆነ ይጠቅሳሉ። ብሪጅም፣ ይኽን አነስተኛ ሊባል ቢችልም፣ መፍትሔ ቢበጅለት ለአገራዊ የዲሞክራሲ ተቋም ግንባታ ኹሉን አሳታፊነት ድርሻው ብዙ ነውና፣ እንደራሴዎቹም ሆኑ ይመለከታቸዋል የሚባሉት የምክር ቤቱ የውስጥ ተቋማት አበክረው እንዲያስቡበት ስትል ብሪጅ ማስታወስ ትፈልጋለች።

# መጠቅለያ. . .

አኹን በሥራ ላይ ያለው ፩ኛው የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ከቀደሙት አምስት ምክር ቤቶች የተሻሉ የሕዝብ ውክልና ሥራዎችን ተግብሯል። ከምክር ቤቱ ዐቅም ውጪ ባሉ ምክንያቶች እንደራሴዎቹ መድረስ ያልቻሉባቸው ጥቂት አካባቢዎች ቢኖሩም፣ ኹሉም ሊባሉ በሚችሉት የፌዴሬሽኑ ክልሎች ውስጥ የሕዝብ ውክልና ሥራዎች በወርኃ የካቲት፣ ነሐሴ፣ ጷግሜ እና መስከረም እና ጥቅምት ጭምር መደረጋቸው ተጠቃሽ ኹነት ነው። ያም ሆኖ፣ የእንደራሴነት መቆሚያ የሕዝብ ውክልና ግብር ነውና፣ ከላይ የጠቀሱት ጥቂትም ቢሆኑ ክፍተት ተድርገው ሊታሰቡ የሚገባቸው ጉድለቶች በዚኽኛው የምክር ቤቱ ቀጣይ የውክልና ክንውን የሚደፈኑበት አግባብ ቢኖር፣ ውክልናውን ይበልጥ ስኬታማ ያደርገዋል። ከዚያ በመለስ፣ በውክልና ሥራዎች ወቅት ለመራጮቹ የሚነሱት ጥያቄዎች እና ችግር መፍቻ አስተያይቶችን፣ ከአንዱ አካባቢ በሌላ አካባቢ ካለው በማንጸር ሰፊ ጥናቶች ቢደረጉ፣ በተለይም ለፖሊሲ አውጪዎቹ እና ሥራ አሥፈጻሚው ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል። ከዚኽ ባለፈም፣ የእንደራሴዎቹ ተከታታይነት ያለው ያልተቋረጠ የሥራ አሥፈጻሚው ቁጥጥር ከዚኽ ይበልጥ ተጠናክሮ ቢቀጠል፣ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ግንባታ ፋይዳው የሚናቅ አለመሆኑንም ማስታወስ ያሻል።

## ፍካሬ ዘ እንደራሴ

“እንደራሴ” የሚለው ንባበ-ቃል በኢትዮጵያ ጥንታዊ እና ዘመናዊ የፖለቲካ ተዋስዖ እና የሥነ-መንግሥት ታሪክ ውስጥ ግዝፈት የነሳ ፍካሬያዊ ንባበ-ቃል ነው። የቃሉ ከየት መጥነት እና ፍካሬም፣ በአጠቃሎ መልኩ ይኽን መሰል ፍቺዎች ነበሩት/አሉትም።

ንባበ-ቃሉ የተገኘው “እንደ” እና “ራሴ” ከሚሉ የኹለት ቃላት ጥምረት ነው። “እንደ”፦ መስያ፣ ፈንታን ወይም ምትክን ሲያመለክት፤ “ራሴ”፦ ራስ ጠሪውን ማንነት አልያም ባለቤቱን-ሲፈከርም ባለሥልጣኑን ያነጽራል። በአማሪያዊ ፍቺውም፣ “እንደ እኔ” ወይም “እኔን ሆኖ” ማለት ነው ይሏል። በኢትዮጵያ ሥነ-መንግሥት ታሪክ “እንደራሴ” የሚለው ማዕረግነቱን ሲያጣቅስ፣ በተለያዩ ዘመናት የተለያየ ማኅበረ-ፖለቲካዊ ትርጓሜ ነበረው፤ ለማሳያ፦

ሀ- የንጉሠ ነገሥቱ ተወካይ (በፈረንጅ አፍ- Regent እንዲሉ)፦ በንጉሣዊው ሥርዓት ዘመን ንጉሠ ነገሥቱ በአንዳች ምክንያት (ለዐቅመ-መንበር ባለመድረስ፣ በሕመም ወይም በሌላ ምክንያት) አገረ-መንግሥቱን መምራት ካልቻሉ፣ ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቶት አገሪቱን የሚያሥተዳድረው ሰው “ቢትወደድ-እንደራሴ” ይባል ነበር።

ለ- የአካባቢ ወይም የክፍለ-ሀገር ገዢነት፦ ንጉሠ ነገሥቱ በየክፍለ ሀገራቱ ‘ራሳቸው ዘወትር መገኘት ስለማይችሉ፣ በ‘ርሳቸው ስም የሚፈርዱ እና የሚያሥተዳድሩ ተወካዮቻቸውን “እንደራሴ” ይሏቸዋል፤ ይኽም የንጉሡ ምሉዕ ተወካይነትን ይሰጣል።

ሐ-የሕዝብ እንደራሴነት፦የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ከመጣ ወዲኽ ግን ቃሉ አዲስ ፍካሬ ያዘ። ሕዝቡ በ‘ራሱ ፈንታ ሆኖ በምክር ቤት እንዲመክርለት እና ውሳኔም እንዲሰጥለት የሚመርጣቸው ሰዎች “የሕዝብ እንደራሴዎች” መባል ጀመሩ። የዚኽ ፍካሬም፣ “ሕዝቡን ሆኖ የሚሠራ”፣ “ምስለ-ሕዝብ” አልያም “የሕዝቡ ተወካይ” የሚል ትርጓሜን አሰጠው።

ዛሬ “ተወካይ” (በምዕራቡ የምክር ቤት ታሪክ ጅማሮ-Representative-እንዲሉ) ከሚለው ቃል ጋር መሳ ለመሳ ሆኖ ያገለግላል። ሆኖም “እንደራሴ” የሚለው ቃል ከውክልና ባለፈ፣ የወከለውን አካል ሙሉ ክብር እና ማንነታዊ ተዛምዶ ይዞ የሚገኝ ክብደት ያለው ፖለቲካዊ እና ማኅበረ-ባህላዊ ፍካሬ አለው።

## የብሪጅ አፈካከር

ተቋማችን ብሪጅ፣ የአማርኛን ሰዋስው ደንብ ጠብቃ፣ ይኽንን ቃል ከኋለኛው ወደዚኽ ዘመን አናጥቃ በመፈከር ተጠቅማለች። አስቀድመን ሊቃውንቱ ያስቀመጡትን እንጥቀስ፤ ደስታ ተክለ ወልድ፣ እንደ ራሴ፣ እኔን ሆኖ፣ የእኔን ሥልጣን ይዞ የሚሠራ ብለው ሲፈቱት፤ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ በፈንታ፣ በምትክ የሚቆም ሲሉት፤ ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጸው በተራቸው፣ ተለዋጭ፣ ተወካይ፣ ባለሙሉ ሥልጣን የሚል ፍቺ ይሰጡታል። ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀልም ቢሆኑ፣ አንድ ሰው በራሱ ስም ሳይሆን በሌላው ስም ተገኝቶ የሕግ ተግባራትን ሲያከናውን እንደራሴ መባሉን ያነሳሉ። እነዚኽ ዋቢዎች እንደሚያሳዩት፣ ቃሉ በመጀመሪያ ለነገሥታት ተወካዮች ብቻ ይሠራበት የነበረ ሲሆን፣ ኋላ ለሕዝብ ተወካዮች እንዲሠራበት የተደረገው የሕዝቡን ልዕልና ለመግለጽ ውለዋል፤ አለፍ ሲልም፣ ተወካዩ ሕዝቡን ሆኖ ይገኛል፤ እንደ ሕዝቡ ሆኖ ይጠራል የሚለውን ፍካሬ ይሰጣሉ።

በዚኽ አግባብ፣ “እንደራሴ” ስንል፦ አንድም ራስ የሚለውን የኢትዮጵያ ፌዴሬሽን ከቆመበት ‘የራስን ዕድል በራስ የመወሰን’ ሕገ-መንግሥታዊ ነባር መርህ ጋር አናጽረን ፈክረነዋል። ይኽ ማለት፣ በዚኽ መርህ ውስጥ ያለው ‘ራስ’፣ የሚለው ትርጉም የሚጠቅልላቸውን ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፣ በ “እንደራሴ” ውስጥ ያለውን ‘ራሴ’ን ለመፍታት ፍካሬያዊ ትርጓሜን ተጠቅመናል። ከዚያ ባለፈም፣ በቀደመው ዘመን መራጩ ንጉሠ ነገሥቱ እንደሆነው ሁሉ፣ በዚኽኛው የእኛው ዘመን ሕዝብ ነውና፣ “እንደራሴ” ስንል፦ እንደ መረጠው ሕዝብ፣ ብሔረሰብ አልያም ብሔር የሆነ በሚል ፍቺ መጠቀማችንን ልብ ይሏል። በዘመናዊው የምርጫ ሥርዓት ስናነጽረውም፣ መራጩ ግለሰብ እንደራሴውን ‘ተናገር በከንፈሬ፣ ተቀመጥ በመንበሬ’ ሲል፣ በነገረ-ሕይወቱ ይወስንለት ዘንድ ወደ ምክር ቤቱ መርጦ ይልከዋል። የመረጠውም እንደራሱ ካልሆነለት፣ ምስለ እኔነቱን ሊነጥቀው መቻሉን ያስረግጣል።

የ“እንደራሴ” ንባበ-ቃል፣ ምንም እንኳን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ሲቋቋም፣ የምክር ቤቱ የሥራ ቋንቋ በዘመኑ ብሔራዊ ቋንቋ የነበረው አማርኛ ብቻ ቢሆንም ቅሉ፣ ንባበ-ቃሉ ግን በሌሎቹ የአገራችን የብሔር ብሔረ ሰቦች ቋንቋዎች ውስጥም መገኘቱን ልብ ይሏል፤ ለማሳያ፦ በሲዳማ- amaalete mina፣ በአፋን ኦሮሞ-Bakka bu’aa፣ በትግሪኛ- ከማይ፣ በወላይተኛ Kal Atiya/Taga ton መባሉን ያስታውሷል።

### ከራስ ውርድ፦

“በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።”

# እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

**BRIDGE** Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 911 86 12 34

research@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.